# ክፍለ ትምህርት አንድ

## 1. እኛነታችን

### 1.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን


- ጉልበት
- ጡንቻ
- ጭን
- መዳፍ
- ቁርጭምጭሚት
- ቅልጥም

**መታወቅ የሚገባቸው ቃላት**

- መጉመጥመጥ
- ንጽሕና
- ጥገኛ
- ውበት
- ብሩሽ

### 1.1.1. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች

**የሰው ውጫዊ አካል ክፍሎች ምን ምን ተብለው ይጠራሉ ?**




ሥዕል 1.1. የሰው ውጫዊ የአካል ክፍሎች

**መልመጃ 1.1.**

ሀ/ ስዕሉን በማየት ከአንገት በላይ ያሉትን የአካል ክፍሎች ከሚያመለክቱት ቁጥሮች ጋር አዛምዱ፡፡

ምሳሌ ፡- ሀ. ቁጥር 1 ፀጉርን ያመለክታል፡፡

ለ. ቁጥር 2 ዓይንን ያመለክታል

ሐ. ቁጥር _________ ጉንጭን ያመለክታል፡፡

መ. ቁጥር _________ ራስን ያመለክታል፡፡

ሠ. ቁጥር _________ ጆሮን ያመለክታል፡፡

ረ. ቁጥር _________ ቅንድብን ያመለክታል፡፡

ሰ. ቁጥር _________ አፍንጫን ያመለክታል፡፡

ሸ. ቁጥር _________ ግንባርንያመለክታል፡፡

ቀ. ቁጥር _________ ከንፈርን ያመለክታል፡፡

በ. ቁጥር _________ አገጭን ያመለክታል፡፡

ተ. ቁጥር _________ አንገትን ያመለክታል፡፡

ለ/ ስዕሉን በማየት ከአንገት በታች ያሉትን የአካል ክፍሎች ከሚያመለክቱት ቁጥሮች ጋር አዛምዱ፡፡

ሀ. __________ትከሻ ነው፡፡

ለ. __________የእጅ ጡንቻ ነው፡፡

ሐ. __________ክንድ ነው፡፡

መ. __________ጭን ነው፡፡

ሠ. __________ሆድ ነው፡፡

ረ. __________ደረት ነው፡፡

ሰ. __________መዳፍ ነው፡፡

ሸ. __________የእጅ ጣት ነው፡፡

ቀ. __________ ጉልበት ነው፡፡

በ. __________ ቁርጭምጭሚት ነው፡፡

ተ. __________ቅልጥም ነው፡፡

ቸ. __________የእግር ጣት ነው፡፡

## 1.1.2. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች አገልግሎት

- አይን ለምን ይጠቅማል?
- ጆሮ ለምን ይጠቅማል?
- አፍንጫ ለምን ይጠቅማል?


ሀ.



ለ.



ሐ.



### 1.2. የአንዳንድ የአካል ክፍሎች አገልግሎት

ከላይ የተቀመጡትን ስዕሎች በመመልከት የሚሰጡትን ጥቅም ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

1. ሥዕል “ሀ” የሚያሳየው  የትኛውን የሰውነት የአካል ጥቅም ነው?

2. ሥዕል "ለ" ከሚያሳየው የአካል ክፍላችን ምግብ ለመብላት የሚያገለግለን የትኛው ነው?

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የአካል ክፍሎች አገልግሎት ተናገሩ፡፡

ሀ. አንገት

ለ. ፀጉር

ሐ. አይን

መ. ጆሮ

ሠ. አፍንጫ

**ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን መጠበቅ**

የሰውነት ክፍሎቻችንን ንፅሕና መጠበቅ ለምን ያስፈልጋል?
የአካል ክፍሎቻችን የተሟላ ሥራ እንዲሰሩ ንፅሕናቸው በሚገባ መጠበቅ አለበት፡፡
የአካል ክፍሎቻችሁን ንፅሕና የምትጠብቁት እንዴት ነው?
የአካል ክፍሎቻችሁን ንፅሕና ለመጠበቅ ምን ምን ትጠቀማላችሁ?



ጠዋት ጠዋት ከመኝታችን እንደተነሳን እጃችንንና ፊታችንን በሳሙናና በንፁህ ውሃ መታጠብ አለብን፡፡

ፊትን በየእለቱ መታጠብ ተገቢ ነው፡፡



ምግብ ከተመገብን በኋላ አፋችንን በንፁህ ውሃ መጉመጥመጥ አለብን። በጥርሶቻችን መሀከል የቀረውን ምግብ በባሕላዊ ወይም በዘመናዊ መፋቂያ ማስወገድ ያስፈልጋል። በተጨማሪ ዘወትር ጠዋት ጠዋት የጥርሳችንን ንጽሕና መጠበቅ አለብን።

ጥርስን በየዕለቱ ማጽዳት ያስፈልጋል።



ፀጉርን በየጊዜው መታጠብ ተገቢ ነው



ፀጉራችን በየቀኑ መበጠር አለበት፡፡

- ቅማል፣ ቅጫምና የመሳሰሉት ጥገኛ ሕዋሳት ምን ዓይነት ጉዳቶችን ያስከትላሉ?
    - በሽታን ከሰው ወደ ሰው ያሰተላልፋሉ፡፡
    - በቆዳችን ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡
    - ደማችንን ይመጣሉ፡፡
- የፀጉርን ንፅሕና ስንጠብቅ፡-
    - የተሟላ ጤንነት ይኖረናል፡፡
    - ውበታችንን ለመጠበቅ ይረዳናል፡፡



በአፍንጫ ቀዳዳ አቧራ ገብቶ በሽታ
ሊያስከትል ይችላል። ስለዚህ
አፍንጫን በንፁህ መሀረብ ወይም
ጨርቅ ማፅዳት ያስፈልጋል።

አፍንጫ በንፁህ መሀረብ መፅዳት አለበት።



ምግብ ሲቀርብላችሁ መጀመሪያ ምን ታደርጋላችሁ?





**የገላችን ንፅሕና መጠበቅ አለበት፡፡**

ገላችንን በየጊዜው ካልታጠብን፡-

- ለበሽታ ያጋልጠናል፡፡
- ውበታችንን ይቀንሰዋል፡፡
- መጥፎ ጠረን ይኖረናል፡፡

ስለዚህ ልጆች ! በየጊዜው የሰውነታችንን ንፅሕና መጠበቅ አለብን፡፡



እግርን በየቀኑ መታጠብ ያስፈልጋል፡፡

- እግር በየቀኑ መታጠብና ንፅሕናውን መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡ እግራችንን ያለመታጠብ መጥፎ ሽታ ያስከትላል፡፡ በተጨማሪ የእግራችንን ጤንነት ለመጠበቅ ጫማ መጠቀም ያሰፈልጋል፡፡

ጫማ ማድረግ የተለያየ ጠቀሜታ ይሰጠናል፡-

- የመሬት ትላትሎች እንዳይጎዱን ይረዳናል፡፡
- የዛጉና ስለት ያላቸው ነገሮች እንዲሁም እሾህ እንዳይወጋን ይከላከልልናል፡፡
- ድንጋይ /እንቅፋት/ አንዳይመታን ይከላከልልናል፡፡

ስለዚህ ተማሪዎች! ሁልጉዜ ጫማ ማድረግ አለብን ማለት ነው፡፡



በየሳምንቱ ጥፍሮቻችሁን መቁረጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ጥፍራችን ሲያድግ በውስጡ ቆሻሻን ስለሚይዝ ምግብ በምንመገብበት ጊዜ ቆሻሻው ወደ ሆዳችን በመግባት ለበሽታ ያጋልጠናል፡፡

ጥፍር ሲያድግ መቁረጥ ያስፈልጋል፡፡

ሥዕል 1.3 የአካል ክፍሎች ንፅህና አጠባበቅ፡፡

የአካል ክፍሎቻችንን ንፅሕና ካልጠበቅን በተለያዩ በሽታዎች ልንጠቃ እንችላለን፡፡

በአካባቢያችሁ የአካል ክፍሎችን ንፅሕና ባለመጠበቅ የሚመጡ በሽታዎች ምን ምን ናቸው? ለመምህራችሁ ተናገሩ ፡፡

**መልመጃ** 1.2.

**ሀ. ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. ከምግብ በፊትና ከምግብ በኋላ እጅን መታጠብ አስፈላጊ ነው፡፡
2. ጥፍሮቻችን ቢያድጉ በጤናችን ላይ ችግር አያመጡም፡፡
3. የአይናችንን ንፅሕና ለመጠበቅ ፊታችንን ጠዋትና ማታ መታጠብ ያስፈልጋል፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

4. የአፍንጫችንን ንፅሕና እንዴት እንጠብቃለን?
   ሀ/ በማሸት  ለ/ በመሃረብ በመጥረግ  ሐ/ በመጎርጎር  መ/ በማከክ
5. ከአንገት በላይ ያለው የሰውነት ውጫዊ አካል የቱ ነው?
   ሀ/ ሆድ  ለ/ እግር  ሐ/ ደረት  መ/ አፍንጫ
6. ውጫዊ የሰውነት ክፍል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ/ እግር  ለ/ ደረት  ሐ/ ሆድ  መ/ ሁሉም

## 1.2.መሰረታዊ ፍላጎቶቻችን

- ምግብ
- ልብስ
- መጠለያ

**መታወቅ የሚገባቸው ቃላት**

- ጣዕም
- ጠጣር
- መዓዛ
- ፍላጎት
- ሻካራ
- ለስላሳ
- ቁሳቁስ
- ወቅት
- አውሬ
- ኩዋሻኮር
- እንቅርት
- ወረሀ

### 1.2.1. ሦስቱ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶች

- የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ምን ምን ናቸው?

እስቲ ልጆች! ቀጥሎ በቀረበው ስዕል የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ምን ምን እንደሆኑ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡



ሥዕል 1.4 የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች

ሦስቱ የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች፡-

ሀ. ምግብ

ለ. ልብስ

ሐ. መጠለያ ናቸው፡፡

### 1.2.2. የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ጠቀሜታ


**ሀ/ ምግብ**

ምግብ ምንድነው?

ምግብ ማለት የሚበላና  የሚጠጣ በጠጣርና በፈሳሽ መልክ የሚገኝ ምግብ ይባላል፡፡

በአካባቢያችሁ በአብዛኛው የምትመገቡት የምግብ ዓይነት ምንድነው?

ዘርዝራችሁ ንገሩዋቸው፡፡





ሥዕል 1.5. የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች

ምግብ ለምን እንደሚጠቅም ታውቃላችሁ?

ምግብ ለሰውነታችን ምን ጥቅም እንደሚሰጠን የቡድን ውይይት በማድረግ ዘርዝሩ፡፡

የተለያዩ ምግቦችን መመገብ፡-ጤንነታችንን ይጠብቃል፡፡


- የተስተካከለ አካላዊ ዕድገት እንዲኖረን ያግዛል፡፡
- ከባድና ቀላል ስራዎችን ለመስራት ይረዳናል፡፡



ሥዕል 1.6 በሽታ ተከላካይ ምግቦች

አንድ ሰው ጤነኛ ሆኖ ለመኖር ምን ምን አይነት ምግቦችን መመገብ አለበት?

ለጤንነት የሚያስፈልጉ ምግቦችን በየዕለቱ መመገብ አለብን፡፡ ለጤንነት የሚያሰፈልጉ ምግቦችን የማይመገብ ሰው ለምግብ እጥረት በሽታ ይጋለጣል፡፡ ለምሳሌ፡- ኩዋሽኮር፣ አንቅርት፣ ወረሀነትና የመሳሰሉትን አይነት ማለት ነው፡፡






የኩዋሽኮር በሽታ የያዘው ሕጻን

የእንቅርት በሽታ የያዛት ሴት

ሥዕል 1.7 በምግብ ዕጥረት የሚመጡ በሽታዎች


ሰውነታችንን ከሚገነቡ የምግብ ዓይነቶች ጥቂቶቹን ተናገሩ ፡፡





ሥዕል 1.8 ለዕድገትና ለአካል ግንባታ የሚረዱ ምግቦች

ምግብ ለተስተካከለ እድገት አስፈላጊ ነው፡፡

ኃይልና ጉልበት ከሚሰጡ የምግብ አይነቶች ሦስቱን ጥቀሱ፡፡



ሥዕል 1.9 የኃይልና ጉልበት ሰጪ ምግቦች



ሥዕል 1.10 ምግብ የተለያዩ ስራዎችን ለማከናወን ይረዳል፡፡


## ለ. ልብስ

ልብስ ከሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶች አንዱ ነው፡፡

ልብስ ለምን ለምን ይጠቀማል?

ልብስ ከምን ከምን ይሰራል?

የለበሳችሁት ልብስ ከምን እንደተሰራ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡



ሥዕል 1.11 የልብስ ዓይነቶች

ልብስ ከጥጥ፣ ከሱፍ፣ ከቆዳና ከላይለን ይሰራል፡፡

የልብስ ጥቅም ፡-

1. ከብርድ፤ ከፀሐይና ከዝናብ ለመከላከል ይጠቅማል፡፡
2. ውበትን ለመጠበቅ /ለማጌጥ/ ይጠቅማል፡፡

ከቆዳ ምን ዓይነት ልብስ ይሰራል?



ጃኬት



ሱፍ ከበግ ፀጉር የሚገኝ

ሲሆን የተለያዩ ልብሶች

ይሰራበታል፡፡

ሥዕል 1.12 ከተለያዩ ነገሮች የሚሰሩ ልዩ ልዩ ልብሶች


የልብስ ባሕሪያት ሁለት አይነት ናቸው፡፡

1. ሻካራ
2. ለስላሳ

- ከውስጥ የሚለበሱ ልብሶች ለስላሳ መሆን አለባቸው፡፡
- ሻካራ ልብሶች ደግሞ ከላይ የሚለበሱ መሆን አለባቸው፡፡
- ብርድና ቅዝቃዜ ባለበት ቦታና ወቅት ከሱፍ የተሰሩ ወፍራም ልብሶችን መልበስ ያስፈልጋል፡፡
- በሞቃት ጊዜና ቦታ ስስና ቀለል ያሉ ልብሶችን መልበስ ይጠቅማል፡፡

ሐ/ መጠለያ

- መጠለያ ከምን ከምን እንደሚሰሩ ዘርዝሩ፡፡
- በአካባቢያችሁ በብዛት የተለመዱ የመጠለያ ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው?
- መጠለያ ለምን ይጠቅማል?



ሥዕል 1.13 የመጠለያ ዓይነቶችና የተሰሩባቸው ቁሳቁሶች

የሰው ልጅ መጠለያዎች ወይም ቤቶች በዋናነት የሚሰሩት ፦

- ከእንጨት
- ከሳር
- ከጭቃ
- ከቆርቆሮ
- ከሸክላ
- ከብሎኬትና ከመሳሰሉት ነው፡፡

የመጠለያ ጥቅም ፦

መጠለያ ለሰው ልጅ ልዩ ልዩ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡



ሥዕል 1.14 የመጠለያ ጥቅሞች

መጠለያ ፡-

- ከዝናብ
- ከፀሐይ
- ከአውሬ ለመከላከል ይጠቅመናል፡፡

በተጨማሪስ ምን አይነት አገልግሎት ይሰልጣል? ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

የሰው ልጅ ከመሰረታዊ ፍላጎቶች አንዱ ባይሟላ ምን ዓይነት ችግር ሊያጋጥመው ይችላል?

የሰው ልጅ ፡- የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን የማያገኝ ከሆነ፡-

- የተስተካከለ እድገት አይኖረውም፡፡
- ጉልበት ያጣል፡፡
- ለተለያዩ በሽታዎች ይጋለጣል፡፡

የሰው ልጅ ፡- ልብስ ባይኖረው

- ለብርድ /ለቅዝቃቄ/ ይጋለጣል፡፡
- ለዝናብ ይጋለጣል፡፡
- ለፀሐይ ጨረር ይጋለጣል፡፡

የሰው ልጅ ፡- መጠለያ ባይኖረው

- ለፀሐይና ለዝናብ እንዲሁም ከተለያዩ አውሬዎች ጥቃት ይደርስበታል፡፡

**መልመጃ 1.3**

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ከሚከተሉት የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎት ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ/ ምግብ ለ/ ልብስ ሐ/ መጠለያ መ/ መልሱ የለም

2. ምግብ ለምን ይጠቅማል?

   ሀ/ ለጤንነት ለ/ ለተስተካከለ ዕድገት

   ሐ/ ለብርታት መ/ ሁሉም

3. የልብስ ጥቅም የትኛው ነው ?

   ሀ/ ለአካል ግንባታ ለ/ ለብርታት ሐ/ ለውበት መ/ ለእድገት

4. ከሚከተሉት ውስጥ በፀሐይ ወቅት የሚለበሰው የትኛው ነው ?

   ሀ/ ሸሚዝ ለ/ ጋቢ ሐ/ ሹራብ መ/ ብርድ ልብስ

5. ከሚከተሉት ውስጥ ለመጠለያነት የሚያገለግለው የትኛው ነው?

ሀ/ ሳር ቤት ለ/ ቆርቆሮ ቤት ሐ/ የሸክላ ቤት መ/ ሁሉም

**ለ/ ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

6. ምግብ በሕይወት ለመኖር አስፈላጊ ነው፡፡

7. የዝናብ ልብስ ሁልጊዜ ይለበሳል፡፡

8. ጫማ ፣ ጃኬትና ቀበቶ ከቆዳ መስራት ይቻላል፡፡

**በተደጋጋሚ የሚያጠቁን በሽታዎች**

| መታወቅ የሚገባቸው ቃላት | |
|---|---|
| - በሽታ | - ልቅ |
| - ጤና | - አኅበር |
| - ትኩሳት | - ረግረግ |
| - መንቀጥቀጥ | - መፀዳጃ |
| - ሕዋስ | - ሽታ |
| - መንስኤ | |

### 1.3.1. በተደጋጋሚ በመከሰት የሚታወቁ የተለመዱ በሽታዎች

በአካባቢያችሁ የምታውቁት በተደጋጋሚ የሚከሰቱ በሽታዎች ምን ምን ናቸው? ቤተሰቦቻችሁም

ሆነ እናንተ በየትኛው የበሽታ አይነት ተጠቅታችሁ ታውቃላችሁ?

በተደጋጋሚ የሚያጠቁን በሽታዎች እንደ ጉንፋን፣ ወባ፣ተቅማጥና ወስፋት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ሀ. ጉንፋን፡

- ጉንፋን የሚተላለፍባቸው መንገዶች ምን ይመስሏችኋል?
- የጉንፋን በሽታ ምልክቶች ምን ምን ናቸው? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩዋቸው፡፡



ሥዕል 1.15 በጉንፋን በሽታ የተያዘ ሰው


ጉንፋን ተላላፊ በሽታ ነው፡፡

- የሚተላለፍባቸው መንገዶች ወይንም ሊይዘን የሚችለው፡-
    - በትንፋሽ ከሰው ወደ ሰው፣
    - ከቆሻሻ /በመጥፎ / ሽታ፣
    - ከአፍና ከአፍንጫ በሚወጣ ፈሳሽ እንዲሁም
    - መጠጫዎችን በጋራ በመጠቀም ነው፡፡
- የጉንፋን በሽታ ምልክቶች
    - ትኩሳት /ራስ ምታት/
    - ሣል
    - ከአፍንጫ ፈሳሽ መውጣት ናቸው፡፡

**ለ/ የወባ በሽታ**

የወባ በሽታ መተላለፊያ መንገዱ ምንዱነው?

የወባ በሽታ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?





ሥዕል 1.16 የወባ በሽታ መተላለፊያና መራቢያ ቦታዎች

የወባ በሽታ በወባ ትንኝ ንክሻ የማመጣ በሽታ ነው፡፡

የወባ በሽታ ምልክቶች ፡-

- ትኩሳት
- ማንቀጥቀጥ
- ማቅለሽለሽ ወይም የምግብ ፍላጎት መቀነስ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**ሐ/ ተቅማጥ**

የተቅማጥ በሽታ በሰው ላይ ምን ዓይነት ጉዳት የሚያስከትል ይመስላችኋል?
የተቅማጥ በሽታ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

የተቅማጥ በሽታ በጥቃቅን /በአይን በማይታዩ / ሕዋሳት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡

የተቅማጥ በሽታ መንስኤዎች ፡-

- የተበከለ ምግብ በመመገብ
- የተበከለ ውሃ ወይም ንፅህናው ያልተጠበቀ ውሃ በመጠጣት

- የአካባቢንና የግል ንፅሕናን ባለመጠበቅ
- ንፅሕናው ባልተጠበቀ የመመገቢያ ዕቃ በመጠቀም ናቸው፡፡

የተቅማጥ በሽታ ምልክቶች ፡-


- የሆድ ሕመም፣
- ትኩሣት፣
- ቀጭን አይነምድር የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**መ/ ወስፋት**

ወስፋት የሚባለው በአንጀታችን ውስጥ ሊኖር የሚችል ጥገኛ ትል ነው፡፡ ይህም ትል በአንጀታችን ውስጥ ያለውን የተጣራ ምግብ በመሻማት ይጎዳናል፡፡ የወስፋት በሽታ መተላለፊያ መንገዶች የተበከለ ውሃ በመጠጣትና የተበከለ ምግብ በመመገብ ነው፡፡

ምልክቶቹም፡-

- ማቅለሽለሽ
- የምግብ ፍላጎት መቀነስ
- መክሳትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡




ሥዕል 1.17 የወስፋት ትል

## 1.3.2 ኤድስ


ኤድስ ምንድነው?

የኤድስን በሽታ የሚያመጣው ሕዋስ ምን ይባላል?

የሰውነት የመከላከያ አቅምን በማዳከም ለሞት የሚዳርግና መድሃኒት የሌለው ገዳይ በሽታ ነው፡፡ መንስኤውም ኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ የተባለ ሕዋስ ነው፡፡ ኤች አይ ቪ ቫይረስ በሰውአካል ውስጥ በሽታን ለመከላከል የሚያስችለውን የአካል ክፍል በማዳከምና በመጉዳት የሚያጠቃ ሕዋስ ነው፡፡



ሥዕል 1.18 ከኤድስ መተላለፊያ መንገዶች አንዱ፤ሰው የጥርስ ብሩሽ ሌላው ሲጠቀም ነው፡፡



ሥዕል 1.19 ሌላው በተጠቀመበት ጥፍር መቁረጫ መጠቀም ተገቢ አይደለም፡፡



ሥዕል 1.20 ባልፀዱ

የሕክምና ዕቃዎች መገልገል ለኤድስ በሽታ ያጋልጣል፡፡

ሌሎች የበሽታው መተላለፊያ መንገዶችም አሉ፡፡ ይኸውም፡-

- ልቅ በሆነ ግብረ ስጋ ግንኙነት
- በወሊድ ጊዜ ጥንቃቄ በጎደለው ወሊድ  ከእናት ወደ ልጅ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

ተማሪዎች ጥንቃቄ የጎደለው ወሊድ ምን ማለት ይመስላችኋል?


እናትየው በባሕላዊ አዋላጅ ከተገላገለች የሕፃኑ እትብት በምላጭ በሚቆረጥበት ጊዜ በደም ንክኪ ከእናት ወደ ልጅ በሽታው ሊተላለፍ ይችላል ማለት ነው፡፡


አንዱ በተጠቀመበት መሳሪያ ሌላው ቢጠቀም ለኤድስ በሽታ ያገልጣልን?

የኤድስ በሽታ የማይተላለፍባቸው መንገዶች




ሥዕል 1.21 በወባ ትንኝ ንክሻ ኤድስ በሽታ አይተላለፍም፡፡





ሥዕል 1.22 በመጨባበጥ የኤድስ በሽታ አይተላለፍም፡፡

ሥዕል 1.23 አብሮ በመመገብ የኤች አይ.ቪ. ቫይረስ አይተላለፍም፡፡



ሥዕል 1.24 አብሮ በመጫወት የኤድስ በሽታ አይተላለፍም፡፡

የኤድስ በሽታ መድሃኒት የለውም፡፡ በበሽታው የተያዘ ሰው መዳን ስለማይችል ለሞት ይዳረጋል፡፡ በበሽታው ላለመያዝም የተለያዩ የመከላከያ መንገዶች አሉ፡፡ ይኸውም፡-

- አንዱ የተጠቀመበት ስለት ነክ መሣሪያዎች ሌላ ሰው እንዳይጠቀምባቸው በማድረግ
- በደንብ ባልተቀቀሉ የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ባለመገልገል
- በጋራ የጥርስ ብሩሽ ባለመጠቀም መከላከል ይቻላል፡፡


### 1.3.3. በሽታ መከላከል


ከተላላፊ በሽታዎች ራሳችሁን እንዴት  መከላከል ትችላላችሁ?



አፍን በንፁህ መሀረብ ሸፍኖ መሳል የጉንፋን በሽታ ከአንዱ ወደ ሌላው እንዳይተላፍ ይረዳል፡፡


ሥዕል 1.25 የጉንፋን በሽታ መከላከል







1.26 ንፁህ ሽንት ቤት በመጠቀም የተቅማጥ በሽታን መከላከል ይቻላል፡፡

- መፀዳጀ ቤትን በተገቢው ሁኔታ በመጠቀም
- በንጽሕና በመያዝ ፣
- ከተፀዳዳን በኋላ እ□ችንን በሳሙናና በውሃ በመታጠብ የተቅማጥ በሽታን መከላከል ይቻላል፡፡



ሥዕል 1.27 አጎበር በመጠቀም ከወባትንኝ ንክሻ መከላከል ይቻላል፡፡



ሥዕል 1.28 ረግረጋማ ቦታዎችንበማጽዳት የወባ ትንኝ እንዳይራቡ በማድረግ በሽታውን መከላከል ይቻላል፡፡

**መልመጃ 1.4**

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ከሚከተሉት አንዱ የጉንፋን በሽታ መተላለፊያ መንገድ ነው፡፡

   ሀ/ በመነካካት   ለ/ አብሮ በመብላት   ሐ/ በትንፋሽ   መ/ ሁሉም

2. ከሚከተሉት አንዱ የወባ በሽታ ምልክት ነው፡፡

   ሀ/ ማንቀጥቀጥ   ለ/ ትኩሳት

   ሐ/ የምግብ ፍላጎት መቀነስ   መ/ ሁሉም

3. ከሚከተሉት ውስጥ በተበከለ ውሃና ምግብ የሚመጣ በሽታ የትኛው ነው?

   ሀ/ ጉንፋን   ለ/ ተቅማጥ

   ሐ/ ኤድስ   መ/ መልሱ አልተሰጠም

**ለ/ ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡**


4. አንድ ላይ በመጫወት ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ አይተላለፍም፡፡
5. አንዱ የተጠቀመበትን የስለት መሳሪየ ሌላው ቢጠቀም ምንም አይነት የጤና አይደርስበትም፡፡

## 1.4. አምስቱ የስሜት ሕዋሳት

| **መታወቅ የሚባቸው ቃላት** |
|---|
| - ባሕላዊ<br>- ዘመናዊ<br>- ተግባር<br>- ብርሃን<br>- አቅጣጫ<br>- ድምጽ |

### 1.4.1 የስሜት ሕዋሳት ስም

- የስሜት ሕዋሳት የምንላቸው ስንት ናቸው
- የስሜት ሕዋሳት ምን ምን እንደሆኑ ታውቋላችሁ? ስማቸውን ዘርዝሩ፡፡




አይን




አፍንጫ



ምላስ



ጆሮ




ቆዳ (እጅ)

ሥዕል 1.29 አምስቱ የስሜት ሕዋሣት


### 1.4.2. የስሜት ሕዋሳት ተግባር

የስሜት ሕዋሶቻችን ምን ምን አይነት ተግባራት ያከናውናሉ?

ተግባራቱን ለክፍል ጉዋደኖቻችሁ ተናገሩ፡፡



አይን ለማየት ይጠቅማል ?



ጆሮ ለመስማት ይጠቅማል



አፍንጫ ለማሽተት ይጠቅማል።



ቆዳ ለመዳሰስ ይጠቅማል።




ምላስ ለመቅመስ ይጠቅማል፡፡

ሥእል 1.30 የስሜት ሕዋሳት ተግባራት

## 1.4.3. አይን

አይን በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮችን ለማየት ይጠቅማናል፡፡ አይናችንን ተጠቅመን አካባቢያችንን ለማየት የብርሃን ምንጭ ያስፈልገናል፡፡


ቀንና ማታ የምንጠቀምባቸው የብርሃን ምንጮች ምን ምን ናቸው? ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡




ኩራዝ



ፋኖስ




የፀሐይ ብርሃን




ጨረቃ



ሻማ




አምፑል



ባትሪ

ሥዕል 1.31 የብርሃን ምንጮች


ቀለማትን ለመለየት የሚጠቅመን የስሜት ሕዋስ የትኛው ነው?



ወተት



የኢትዮጵያ ባንዲራ



አበባ

ሥዕል 1.32 ቀለማትን ማየትና መለየት

**ተግባራዊ ክንዋኔ 1.1**

የተለያዩ ቅጠላ ቅጠሎችንና አበባዎችን በመጠቀም ቀለማትን መስራት የሚያስፈልጉ ነገሮች ፡-

- የተለያዩ የእፅዋት ቅጠሎች
- ሙቀጫና ዘነዘና /ጠፍጣፋ እንጨት፤ ጣውላና ድንጋይ/
- ውሃ
- ጉድጓዳ ሣህን
- ወንፊት /ማጥለያ/
- ስኳር

የአሰራር ቅደም ተከተል

- ቅጠሉን መጨቅጨቅ
- ውሃ መጨመር
- ማጥለል
- ስኳር መጨመር
- ለ24 ሰዓት ቀዝቃዛ ቦታ ማስቀመጥ
- የቅጠሉን ጭማቂ መጠቀም

ውጤት ፡- የቅጠሉ ጭማቂ ምን አይነት ሆነ?

ጭማቂው ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ እንደሌሎቹ ቀለማት በወረቀት ላይ ቆየ?

- ቀይ ፣ ሰማያዊ እና ቢጫ ዋና ዋና ቀለማት በመባል ይታወቃሉ፡፡


### 1.4.4 ጆሮ

ዋና ዋና ድምጾችን መለየት

በመስማት የተለያዩ ድምጾችን መለየት ትችላላችሁ?

ጆሮ ድምፅን ለመስማት የምንጠቀምበት የስሜት ሕዋስ ነው፡፡

በተጨማሪ የምንሰማው ድምፅ ከየትኛው አቅጣጫ እንደመጣ ለመለየት ይረዳናል፡፡





ሥዕል 1.33 የተለያዩ የቤት እንስሳት ድምፅ


የተለያዩ የቤት እንስሳትን ድምፅ ማሰማት ትችላላችሁ? በቡድን በመሆን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሙ፡፡

ማታ ማታ ጅብ ሲጮህ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?


እንደወፍ መጮህ ትችላላችሁ?




አንበሳ



ጅብ



ዝሆን




ወፍ

ሥዕል 1.34 ልዩ ልዩ የዱር እነስሳት ድምፅ ይለያያል፡፡

በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን የዱር እንስሳት ድምጾች አሰሙ፡፡

**የሞተር ድምጾች**

በአካባቢያችሁ የተለያዩ ሞተሮች የሚያመነጩትን ድምፅ አስመስላችሁ አሰሙ፡፡





ሥዕል 1.35 ልዩ ልዩ ሰው ሰራሽ ሞተሮች የተለያዩ ድምጾችን ያመነጫሉ፡፡


**የሙዚቃ መሣሪያ ድምጾች**

በአካባቢያችሁ የሚገኙ የሙዚቃ መሣሪያዎች ምን ምን ናቸው?


የሙዚቃ መሳሪያ ድምጾች ይለያያሉ?





ሥዕል 1.36 ባሕላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች



ሳክስፎን



ጊታር




ትራንፔት

*ሥዕል 1.37 ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች*

*በአካባቢያችሁ ካሉት የሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ የተወሰኑትን ምረጡ፡፡ እነዚህን የመረጣችኋቸውን በአካባቢያችሁ ካሉት ቁሳቁሶች ለመስራት ሞክሩ፡፡*

*የሰራችኋቸውን የሙዚቃ መሳሪዎች በክፍል ውስጥ በማምጣት እየነካካችሁ ድምፅ እንዲያሰሙ አድርጉ፡፡*

**የሰዎች ድምፅ**



ሥዕል 1.38 ሰዎች ሲያዝኑ ያለቅሳሉ።




ሥዕል 1.39 ሰዎች ሲደሰቱ ይዘፍናሉ፡፡

### 1.4.5. ምላስ

የተለያዩ ነገሮች መቅመስ

ሁሉም የምግብ አይነት አንድ አይነት ጣዕም አላቸው?

ሁሉንም ነገር መቅመስ ጥሩ ነው ?




ሥዕል 1.40 በመቅመስ የተለያዩ ጣዕም ያላቸውን ምግቦች መለየት እንችላለን፡፡

በጣም ትኩስ ወይም የሚያቃጥል ምግብ መቅመስ ምን ጉዳት ያመጣል?

ሁሉንም ፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገር መቅመስ ተገቢ አይደለም፡፡

አንድ ነገር ከመቅመሳችን በፊት ለጤና ተስማሚ ወይም ጠንቅ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ማረጋገጥ አለብን፡፡


በጣም ትኩስ እና የሚያቃጥል ምግብ በምላሳችን ላይ ጉዳት ያስከትላል፡፡

### 1.4.6. አፍንጫ

በማሽተት የተለያዩ ነገሮችን መለየት

ሁሉም የሚሸቱ ነገሮች አንድ አይነት ሽታ አላቸው?


ሁሉንም ነገር ማሽተት ለጤና ጥሩ ነው?





ሥዕል 1.41 ጥሩ ሽታ /መዓዛ/ ያላቸው ነገሮች

አበባዎች መልካም ሽታ አላቸው፡፡ ነገር ግን ሁሉንም አይነት አበባ ማሽተት ለጤና ጠንቅ ነው፡፡

**የተለያዩ መጥፎ ሽታ ያላቸውን ነገሮች ዘርዝሩ፡፡**





የሞተ እንስሳ

ንጽሕናው ያልተጠበቀ ሽንት ቤት


ሥዕል 1.42 መጥፎ ሽታ ያላቸው ነገሮች


ሽንት ቤቶች፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች፣ ንፅሕና የጎደለው የጫማ ሽታ፣ ወዘተ. መጥፎ ሽታ አላቸው። እነዚህን ነገሮች ማሽተት ወይም በአካባቢያቸው መጫወት ለከፋ የጤና ችግር ይዳርጋል።

1.4.7 ቆዳ

ነገሮችን መዳሰስ

ተማሪዎች የምታውቋቸውን ለስላሳና ሻካራ የሆኑ ነገሮችን ለመምህራችሁ ተናገሩ።





አሸዋ ሻካራ ነገር ነው።

ጥጥ ለስላሳ ነገር ነው።



በቆዳችን ሞቃትና ቀዝቃዛ ነገሮችን እንለያለን፡፡

ሥዕል 1.43 በመዳሰስ የተለያዩ ነገሮችን ለመለየት እንችላለን፡፡

ቆዳ የተለያዩ ነገሮችን በመዳሰስ የምንለይበት የስሜት ሕዋስ ነው፡፡

በጣም ቀዝቃዛ ወይም በጣም ሞቃት የሆነ ውሃ መንካት ቆዳችንን በመጉዳት ለሕመም ይዳርገናል፡፡

**መልመጃ 1.5.**

**ሀ/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. የሙዚቃ መሳሪያዎችን ድምጾች በጆሮአችን እንለያለን፡፡
2. ጨውንና ስኳርን በጣዕማቸው መለየት እንችላለን፡፡
3. ሽንት ቤት ንፅሕናው ካልተጠበቀ መጥፎ ሽታ አለው፡፡

**ለ/ የሚከተሉትን የስሜት ሕዋሳት ከጥቅማቸው ጋር በማስመር አገናኙ /አዛምዱ/፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዓይን | ሀ. ለመዳሰስ |
| 2. አፍንጫ | ለ. ለመቅመስ |
| 3. ጆሮ | ሐ. ለማሽተት |
| 4. ቆዳ | መ. ለማየት |
| 5. ምላስ | ሠ. ለመስማት |

**ሐ/ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. መጥፎ ሽታ ያለው የትኛው ነው?

   ሀ/ አበባ  ለ/ ሽቶ  ሐ/ የሞተ እንስሳ

2. የስልክ መልዕክት የምንቀበለው በየትኛው የስሜትሕዋሳችን ነው?

   ሀ/ በጆሮ  ለ/ በዓይን  ሐ/በአፍንጫ

3. ብርሃን አመንጭ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ/ ድንጋይ  ለ/ መስታወት  ሐ/ ሻማ

**የክለሳ መልመጃ**

**ሀ/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1 ቁርጭምጭሚት ውጫዊ የአካል ክፍል ነው፡፡

2 ጆሮ ድምፅን ለመስማት አያገለግልም፡፡

3 ኤድስ በሽታ መድሃኒት ያልተገኘለት ገዳይ በሽታ ነው፡፡

**ለ/ የሚከተሉትን በ"<u>ለ</u>" ስር የሚገኙትን ጥያቄዎች ከ"<u>ሀ</u>" ስር ከሚገኙት ጋር አዛምዱ፡፡**

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 4 ኃይልና ብርታት ለማግኘት ይጠቅማል | ሀ/ መጠለያ |
| 5 ውበታችንን ለመጠበቅ ይጠቅመናል | ለ/ ምግብ |
| 6 ከአደገኛ አውሬ ለመከላከል ይጠቅማናል | ሐ/ ልብስ |

**ሐ/ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

7 በሞቃት ወቅት መልበስ የሚገባን ልብስ ምን ዓይነት መሆን አለበት?

   ሀ/ ወፍራም  ለ/ ሻካራ  ሐ/ ስስ

8 ልብስ ከምን ከምን ይሰራል?

   ሀ/ ከቆዳ  ለ/ ከጥጥ  ሐ/ ሁሉም

9 መጠለያ ቤቶች የሚሰሩት ከምን ከምን ነው ?

   ሀ/ ከቆርቆሮ  ለ/ ከሳር  ሐ/ ሁሉም

10 ከሚከተሉተ ውሰጥ አንዱ የወባ በሽታ መከላከያ ዘዴ ነው፡፡

   ሀ/ አጎበር መጠቀም ለ/ በሳሙና መታጠብ  ሐ/ ምግብ መብላት

**መ/ ለማከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡**

11 . ኤች አይ ቪ ኤድስ የማይተላለፍባቸውን መንገዶች ግለፁ፡፡

12 . ከአንገት በታች ያሉትን ውጫዊ የአካል ክፍሎች ዘርዝሩ ፡፡

## ማ ጠ ቃ ለ ያ

ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚያካትቱት፡- ጭንቅላት /ራስ/፣ ፀጉር፣ ጆሮ፣ አይን፣፤ አፍንጫ፣ አፍ፣ እጅ፣ ጣት፣ ደረት፣ ሆድ፣ እግር፣ ጉልበትና ቁርጭምጭሚት ናቸው፡፡

የአካል ክፍሎችን ንፅሕና ለመጠበቅ

- እጅን ፊትንና ገላን በየጊዜው መታጠብ
- ፀጉርን መታጠብና ማበጠር፤
- ጥርስን በዘመናዊ ወይንም በባሕላዊ መፋቂያ ማፅዳት
- ጥፍርን መቁረጥ
- አፍንጫን በመሀረብ ወይም በንፁህ ጨርቅ ማፅዳት፤
- እግርን በየእለቱ በሳሙናና በውሃ መታጠብ

ምግብ፣ ልብስና መጠለያ የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ናቸው፡፡
የተለያዩ ምግቦችን፤ ልዩ ልዩ የልብስ አይነቶችንና የተለያየ ቅርፅ ያላቸውን መጠለያዎች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡
በተደጋጋሚ በማጥቃት የሚታወቁና የተለመዱ በሽታዎች የሚባሉት እንደ ጉንፋን፣ ወስፋት፣ ወባና ተቅማጥ ያሉት ናቸው፡፡ በተጨማሪ ኤድስ መድሃኒት የሌለው ገዳይ በሽታ ነው፡፡

የስሜት ሕዋሳት የምንላቸው ዓይን፣ ጆሮ፣ ቆዳ፣ ምላስና አፍንጫ ናቸው፡፡ እነዚህም የሚሰጡት ጠቀሜታ፡-

- አይን ለማየት
- ጆሮ ለመስማት
- ምላስ ለመቅመስ
- አፍንጫ ለማሽተት
- ቆዳ ለመዳሰስ የሚያገለግሉን የስሜት ሕዋሶቻችን ናቸው፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## 2. ቤተሰቦቻችን

### 2.1. የቤተሰብ አባላት

*መታወቅ የሚገባቸው ቃላት*

| | |
|---|---|
| - ቁጠባ | - ሙያተኛ |
| - የአኗኗር ሁኔታ | - ንብረት |
| - ድርሻ | - ታማኝነት |
| - መረዳዳት | - መተሳሰብ |
| - አርአያ | - መከባበር |
| - አስተዳደር | - ሥነ - ምግባር |
| - ፍቅር | |
| - መስክ | |
| - ምንጭ | |

ቤተሰብ ምን ማለት ነው ?

በየአካባቢያችን የሚኖሩ ሰዎች የየራሳቸው ቤተሰብ አላቸው፡፡ ይህ ቤተሰብ የማህበረሰብ መሰረትነው፡፡



ሥዕል 2.1. የቤተሰብ አባላት

የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች እነማን ናቸው?

ከወላጆቻችሁ ቀጥሎ የቀርብ ዘመዶቻችሁ እነማን እንደሆኑ ተናገሩ ፡፡

### 2.1.1 የቤተሰብ አባላት ዝርዝር

ልጆች! የቤተሰብ አባላት የሚባሉትእነማን እንደሆኑ ዘርዝሩ፡፡

የቤተሰብ አባላት የምንላቸው ወላጆች፣ እህቶች፣ ወንድሞች፣ አክስቶች፣ አጎቶች እና ሌሎችም የቅርብ ቤተሰቦች ናቸው፡፡

**እናትና አባት**

እናትና አባትየልጆች ወላጆች  ናቸው፡፡

እናትና አባት የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች ናቸው፡፡

**ልጆች**

ልጆች! ከእናንተ በፊት ቀድመው የተወለዱና ከእናንተ በኋላ የተወለዱ ወንድም ወይም እህት ምን ብለን እንጠራቸዋለን?

በየአካባቢያችሁ ለሚገኙ ቤተሰቦች መጠሪያ የሆኑ ስያሜዎችን ዘርዝሩ፡፡

ታላቅነትና ታናሽነትየሚገለፅባቸው ሌሎች የአክብሮት መጠሪያዎች አሉ፡፡ እነሱም ጋሼ፣ ወንድምጋሼ፣ እታበባ፣ አባባ፣ እማማ፣ እታለምና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ሴት ልጆች እህት ይባላሉ፡፡ ወንድ ልጆች ወንድም ይባላሉ፡፡



ሥዕል 2.2. ሴት ልጅ



ሥዕል 2.3. ወንድ ልጅ

## ሌሎች የቤተሰብ አባላት

ሌሎች የቤተሰብ አባላት የምንላቸው፡-

- አጎት
- አክስት
- ወንድ አያት እና ሴት አያት ናቸው፡፡

የእናት ወይም የአባት ወንድም አጎት ይባላል፡፡

የእናት ወይም የአባት እህት አክስት ትባላለች፡፡


ልጆች በእድሜ ታናናሽ የሆኑ ልጆች ታላላቅ እህቶቻቸውንና ወንድሞቻቸውን ማክበር አለባቸው፡፡

### 2.1.2. የአኗኗር ሁኔታ

ለመኖር የቤተሰብ አባላት ምን ያደርጋሉ?

እናንተ ቤተሰቦቻችሁን በምን በምን ትረዳላችሁ?

የወላጆቻችሁ የስራ ድርሻ አንድ አይነት ነውን? ለምን? የሥራ ድርሻቸው ምን ምን እንደሆነ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡





ሥዕል 2.4. የቤተሰብ አባላት በስራ ሲረዳዱ

ሴቶችና ወንዶች በማህበራዊ ኑሮ ውሰጥ እኩል የሥራ ድርሻና ኃላፊነት አላቸው፡፡

#### 2.1.2.1. የወላጆች የሥራ ድርሻ /ኃላፊነት/

ወላጆች በቤተሰባቸው ውስጥ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም አለባቸው፡፡

ይኸውም ፡- መልካም አርአያነት

ጥሩ አስተዳደር

እንክብካቤና ፍቅር

**መልካም አርአያነት**

ወላጆች ለልጆቻቸው ጥሩ ነገር እየሰሩ ካስተማሩዋቸው መልካም አርአያነት ይባላል፡፡

**ጥሩ አስተዳደር**

ቤተሰብን በጥሩ ሁኔታ መምራት ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ፡- ልጆችን መቆጣጠር፣ መምከርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**እንክብካቤና ፍቅር**

ወላጆች በአቅማቸው ልጆቻቸውን መርዳትአለባቸው፡፡ ለምሳሌ ፡- ሲታመሙ ማሳከም፣

ደህንነታቸውን መጠበቅ እና ሌሎችም ናቸው፡፡



ሥዕል 2.5. ወላጆች ልጆቻቸውን ሲንከባከቡ

ወላጆቻችሁ በየትኛው የሥራ መስክ ተሰማርተው ይገኛሉ? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩዋቸው፡፡

ስራ ለምን ያስፈልጋል?


ወላጆች እንደ ቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸው ቀጥሎ የቀረቡተን ኃላፊነቶችመወጣት አለባቸው፡፡

- የገቢ ምንጭ መፍጠር
- በገቢ ማስተዳደር
- ቆጥቦ ንብረትን ማፍራት

### የገቢ ምንጭ መፍጠር

ወላጆች የተለያዩ ስራዎችን በመስራት የገቢ ምንጮችን ይፈጥራሉ፡፡ ለምሳሌ ፡- በንግድ፤ በማስተማር፤ በእርሻ ፤ በእጅ ሙያ / እንደ አናፂነት፤ ግንበኝነት/ እንዲሁም የቢሮ ሥራዎችንና ሌሎችንም ያካትታል፡፡

ተማሪዎች! ሌሎች የምታውቋቸውን የሥራ ዘርፎች ለመምህራችሁ ንገሩዋቸው፡፡



ሥዕል 2.6 የተለያዩ የሥራ ገቢ ምንጮች

### በገቢ ማስተዳደር

ወላጅ ባገኘው ገንዘብ ቤተሰቡን ያስተዳድራል፡፡

ለምሳሌ ፡- ለልጆች ልብስ፣ ምግብ፣ ሌላም አስፈላጊ ነገሮችን በመግዛት ሊሆን ይችላል፡፡

ቆጥቦ ንብረት ማፍራት

ተማሪዎች! እርሳስ፣ እስክሪፕቶና ሌሎች የምትጠቀሙበትን ዕቃዎች ሳታባክኑ ትጠቀማላችሁ?

ሳይጠፋባችሁ በደንብ ከተጠቀማችሁ ቆጠባችሁ ይባላል፡፡


ወላጆችም ከሚያገኙት ገንዘብ በማስቀመጥ ቤት ይሰራሉ፣ የቤት ዕቃ ይገዛሉ፣ ይህም ቆጥቦ ንብረት ማፍራት ይባላል፡፡

### 2.1.2.2. የልጆች የሥራ ድርሻ

ልጆች ልክ እንደ እናትና አባት የራሳቸው የስራ ድርሻ አላቸው፡፡

የልጆች የሥራ ድርሻ

- መማር
- የቤተሰብን ደንብ ማክበር
- መታዘዝ






- ቤተሰብን በአቅም መርዳት ናቸው፡፡

ሥዕል 2.7 የልጆች የሥራ ድርሻ

ተማሪዎች! ወደፊት በምን አይነት የስራ ዘርፍ መሰማራት ትፈልጋላችሁ?

ለምን መረጣችሁ? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩዋቸው፡፡

### 2.1.3. የቤተሰብ መልካም ግንኙነት

አንድ ቤተሰብ ጥሩ መሆን የሚችለው በቤተሰብ አባላት መካከል መልካም ግንኙነት ሲኖር ነው፡፡

- ቤተሰባዊ መልካም ግንኙነት የምንላቸው፡-
    - መተሳሰብ
    - መግባባት
    - መፈቃቀር
    - መከባበር
    - በስራ መረዳዳት
    - ችግርን በጋራ መፍታት እና
    - ታማኝነት ናቸው፡፡

መተሳሰብ፡- የቤተሰብ አባላት በመተሳሰብ ይኖራሉ፡፡

መግባባት፡- አንዱ የቤተሰብ አባል ከሌላው የቤተሰብ አባል ጋር ያለው መልካም ግንኙነት መግባባትን ይፈጥራል፡፡

መፈቃቀር፡- አንዱ ለሌላው ጥሩ አመለካከት ካለው የመፈቃቀር ምልክት ነው፡፡

መከባበር፡- በቤተሰብ አባላት መካከል የሚታየው ጤናማ ግንኙነት የመከባበር ውጤት ነው፡፡

ታማኝነት ማለት፡- አለመዋሸት፣

አለመስረቅና፣

አለማታለል ናቸው፡፡



በቤተሰብ ውስጥ ችግር ሲፈጠር በውይይት መፍታት ይገባል።



ለታላቅ ሰው በአክብሮት ሰላምታ መስጠት ያስፈልጋል።

ሥዕል 2.8 የቤተሰብ መልካም ግንኙነት

ታማኝ ልጅ በቤትና በትምህርት ቤት የሚያሳያቸውን ምግባሮች በዝርዝር ተናገሩ፡፡

**መልመጃ 2.1.**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1 ልጆች በአቅማቸው ቤተሰባቸውነ በስራ ማገዝ አለባቸው፡፡

2 ታማኝነት ቤተሰባዊ ሥነ-ምግባር አይደለም፡፡

3 መፈቃቀር የቤተሰብ መልካም ግንኙነት ነው፡፡

**ለ. በ "ለ" ሥር የተቀመጡትን በ "ሀ" ሥር ከተመለከቱት ጋር አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 4 በአንድ ቤተሰብ አባላት መካከል ችግር ሲኖር መፍታት የሚቻለው | ሀ. መማር |
| 5 ከልጆች የሥራ ድርሻ ይመደባል | ለ. የወላጆች ኃላፊነት ነው |
| 6 ቋሚ ንብረት ማፍራት | ሐ. ግብርና |
| 7 የገቢ ምንጭ ማስገኛ ነው | መ. በመወያየት |

**ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውነ መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

8. በታናሽና በታላቅ ልጆች መካከል _______ መኖር አለበት፡፡

ሀ/ መከባበር ለ/ መጣላት ሐ/ መጨቃጨቅ

9. የቤተሰብ አባል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ አባት ለ/ እናት ሐ/ ጎረቤት

10. የእናት ወይም የአባት ወንድም ምን ይባላል?

ሀ/ አያት ለ/ አጐት ሐ/ አባት

## 2.2. የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች

| መታወቅ የሚገባቸው ቃላት |
| --- |
| - እፅዋት<br>- ግብዓት<br>- በጋ<br>- እህል<br>- ምርት |

- የአንድ ቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች የምንላቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡ ይኸውም፡-

1 . ምግብ

2 . ልብስ

3 . መጠለያ


### 2.2.1. ምግብ

የምግብ ምንጭ


በየአካባቢያችን ግብርና ዋና የምግብ ምንጭ ነው፡፡ ግብርና ስንል የእንስሳት እርባታንና የእርሻ ሥራን ያጠቃልላል፡፡

እስቲ በየአካባቢያችሁ የሚበቅሉና ለምግብነትየሚውሉ የእህል አይነቶችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩዋቸው፡፡

በየአካባቢያችሁ የሚበቅሉ ነገርግን ለምግብነት የማይውሉ የእፅዋት አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡



የእንሰት ተክል



የበቆሎ ተክል

ሥዕል 2.9 ለምግብነት የሚውሉ የእፅዋት አይነቶች

**የተለመዱ እህሎች**

በየአካባቢያችን የሚበቅሉና ለምግብነት የሚውሉ የተለያዩ የእህል ዓይነቶች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ፡- ጤፍ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ስንዴ፣ ገብስ የመሳሰሉት ናቸው ፡፡ በተጨማሪ ለምግብነት ከሚውሉ እፅዋት መካከል እንሰት፣ ሙዝ ፣ አቦካዶ፣ ማንጎ፣ ቦይና፣ ጎደሬ ፣ሰኳር ድንች፣ ወዘተ ይገኙበታል፡፡

- በእናንተ ቤተሰብ ውስጥ አዘውትራችሁ የምትመገቡት የምግብ አይነት ምንድነው? ለመምህራችሁ ንገሩዋቸው፡፡
- አዘውትራችሁ ከምትመገቡዋቸው የምግብ አይነት የምትወዱት የትኛውን የምግብ ዓይነት ነው? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩዋቸው፡፡
- በአካባቢያችሁ የእህል ምርት በየትኛው ወቅት ይሰበሰባል?

ሰንጠረዥ 2.1.

ከዚህ በታች በሰንጠረገፉ ውሰጥ ስማቸው የተጠቀሱትን የእህል ምርት ዓይነቶች የሚሰበስቡበት ወቅት መቼ እንደሆነ ከስማቸው አንፃር ጻፉ፡፡

| የእህሉ ዓይነት | የሚሰበሰብበት ወቅት | የእህል ውጤቶች |
|---|---|---|
| በቆሎ | | |
| ጤፍ | | ለእንጀራ |
| ገብስ | | |
| ስንዴ | | |
| ማሽላ | | |

በየአካባቢያችሁ ለምግብነት የማይውሉ /የማይበሉ/ ነገር ግን ለተለያዩ ጥቅም የሚውሉ የእፅዋት አይነቶች አሉን? ካሉ እነማን እንደሆኑ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

ለተለያዩ ጥቅም የሚውሉ እፅዋት ቀርከሃ፣ ዋንዛ፣ ዋርካ፣ የባሕር ዛፍ፣ የወይራ ዛፍ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ለምሳሌ ቀርቀሃ ለቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁስና ለሽመና ሥራ ይውላል፡፡ ባሕር ዛፍ ለቤት መስሪያ ለማገዶነት ያገለግላል፡፡ ዋንዛ ለቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁስ /ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ አልጋ ወዘተ./ ለመስራት ያገለግላል፡፡

### 2.2.2 ልብስ

የልብስ ዓይነት

በእናንተ አካባቢ የሚለበሱ የልብስ አይነቶች ምን ምን አይነቶች ናቸው? የተለያዩ የልብስ ዓይነቶች አሉ፤ እነሱም፡- ኮት፣ ጃኬት፣ ሱሪ፣ ሹራብ፣ ኩታ፣፣ ብረድ ልብስ ጋቢ፣ ሸሚዝ፣ ቡልኮ፣ ቀሚስ፣ ቁምጣና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**ልብሰ ለመስራት የሚያስፈልጉ ግብአቶች /ጥሬ ዕቃዎች/**

ልዩ ልዩ የልብስ አይነቶች ከተለያዩ ግብአቶች /ጥሬ ዕቃዎች/ ይሰራሉ፡፡ እነሱም ፡- ከጥጥ፣ ከሱፍ፣ ከቆዳና ከናይለን ናቸው፡፡


ከእነዚህ ግብአቶች የሚሰሩትን የልብስ አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ለይታችሁ ለመምህራችሁ ንገሩዋቸው፡፡



ከጥጥ የተሰራ ቀሚስ




ከቆዳ የተሰራ ጃኬት



ከሱፍ የተሰራ ብርድ ልብስ

ሥዕል 2.10 ልብሶች ከተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች ይሰራሉ፡፡

ሰንጠረዥ 2.2.

ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የተዘረዘሩት ልብስ ሊሰራባቸው የሚችሉ ጥሬ ዕቃዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ጥሬ ዕቃዎች ምን ምን ዓይነት ልብሶች ሊሰሩ እንደሚችሉ ከፊት ለፊት ባሉት ክፍት ቦታዎች በመፃፍ መልሱ፡፡

| ልብስ ሊሰራባቸው የሚችሉ ጥሬ ዕቃዎች /ግብዓቶች/ | የሚሠራው የልብስ ዓይነት |
|---|---|
| ጥጥ | ጋቢ፣ ነጠላ፣ እንሶላ |
| ሱፍ | |
| ቆዳ | |
| ናይለን | |

በክረምት ወቀትና በበጋ ወቅት የሚለበሱ የልብስ ዓይነቶች አንድ አይነት ናቸው?

በክረምት ጊዜ የሚለበስ የልብስ አይነት በዝናብና በቅዝቃዜ ምክንያት ከባድና /ወፍራም/ ሙቀት ሊሰጥ የሚችል መሆን አለበት፡፡ በበጋ ወቅት ደግሞ ቀላልና ስስ መሆን አለበት፡፡

### 2.2.3. መጠለያ


መጠለያ ለአንድ ቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች ውሰጥ አንዱ ነው፡፡

**የመጠለያ ዓይነቶች**

በየአካባቢያችሁ የሚገኙ የመጠለያ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

በየአካባቢያችሁ የሚገኙ የተለመዱ የመጠለያ አይነቶች ከምን አይነት ቁሳቁሶች እንደተሰሩ ዘርዝሩ፡፡

መጠለያ የምንላቸው ጎጆ ቤት፣ ቆርቆሮ ቤት፣ አፓርታማ ቤቶች ናቸው፡፡




ሥዕል 2.11 የመጠለያ ዓይነቶች

ለቤት ሥራ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነርሱም እንጨት፣ ጭቃ፣ ሳር፣ ድንጋይ፣ ብሎኬት፣ ብረት፣ ቆርቆሮ፣ ሸክላና አልሙኒየም ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ 2.3.

ቀጥሎ በተሰጠው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉትን ለቤት መስሪያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ለምን ሥራ እንደምንጠቀምባቸው ከፊት ለፊታቸው ባሉት ባዶ ቦታዎች ሙሉ፡፡

| የቁሳቁስ አይነት | የሚሰጠው ግልጋሎት |
|---|---|
| ጭቃ | |
| እንጨት | ለግድግዳ |
| ሳር | |
| ድንጋይ | |
| ብሎኮት | |
| ብረት | |
| ቆርቆሮ | |
| ሸክላ | |

**መልመጃ** 2.2.

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1 ግብርና የእንስሳት እርባታና የእርሻ ስራን ያጠቃልላል፡፡

2 ባሕር ዛፍ ለቤትመስሪያ ይጠቅማል፡፡

3 በክረምት ወራት የሚለበስ ልብስ ቀላልና ስስ መሆን አለበት፡፡

4 ድንጋይ ቆርቆሮና ብረት ለቤት መስሪያ አያገለግሉም፡፡

5 ጋቢ እና ኩታ ከጥጥ ይሰራሉ፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡**

6 ከሚከተሉት ውስጥ የአንድ ቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎት የሆነው የቱ ነው?

ሀ/ ምግብ ለ/ ልብስ ሐ/ ሁሉም መልስ ነው፡፡

7 ጫማ የሚሰራው ከምንድነው?

ሀ/ ከቆዳ ለ/ ከሱፍ ሐ/ ከብረት

8 ከሚከተሉት ውሰጥ ለምግብነት የማይወል የእፅዋት አይነት የትኛው ነው?

ሀ/ ገብስ　　　ለ/ በቆሎ　　　ሐ/ ቀርከሃ

9 ከሚከተሉት ውስጥ ለተለያዩ የቤት ቁሳቁስ መስሪያ የሚውል የእፅዋት አይነት የቱ ነው?

ሀ/ ገብስ　　ለ/ ቀርከሃ　　ሐ/ እንሰት

10. ከሚከተሉት ውስጥ መጠለያ ለመስራት የሚየገለግል የትኛው ነው?

ሀ. ጭቃ　ለ. እንጨት　　ሐ. ሁሉም

## 2.3. የቤት ቁሳቁሶች

| መታወቅ የሚገባቸው ቃላት | |
|---|---|
| - መገልገያ | - አያያዝ |
| - መዝናናት | - ጠርሙስ |
| - ማስታወቂያ | - ሸክላ |
| - ሹል | - ጥንቃቄ |
| - ስለት | - |
| - ተፈጥሮ | |

### 2.3.1. የቤት ቁሳቁስ አይነት

ተማሪዎች! በቤታችሁ ውሰጥ የሚገኙትን የተለያዩ የቤት መገልገያ ዕቃዎችን ዘርዝራችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

በኤሌክትሪክ ከሚሰሩ የቤት ቁሳቁስ አይነቶች ውሰጥ ለምሳሌ ፡- ቴሊቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ኤሌክትሪክ የእንጀራ ምጣድ፣ የኤሌክትሪክ ምድጃ ፣ወዘተ. ይገኙበታል፡፡

- ከሸክላ የተሰሩ የዕቃ አይነቶች ጀበና፣ ምጣድ፣ ድስት፣ ወዘተ ናቸው፡፡
- ከእንጨት የተሰሩ ቁሳቁሶች ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ አልጋና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- ከብረትየተሰሩ ቁሳቁሶች ድስት፣ ማንቀርቀሪያ፣ ሹካ፣ ማንኪያና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- ከፕላስቲክ የተሰሩ፡ መመገቢያ ሳህን፣ ኩባያ፣ ማጠቢያና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### 2.3.2. የቤት ቁሳቁስ አገልግሎት

የቤት ቁሳቁስ የምንላቸው፡-


1) ለምግብና ለመጠጥ ማዘጋጃ የሚያገለግሉ
2) ለመመገቢያና ለመጠጫ የሚያገለግሉ

3) ለመቀመጫና ለመኝታ የሚያገለግሉ


4) በቤት ውስጥ ቀላል ሥራ ለመስራት የሚያገለግሉ

5) ለመዝናኛና ማስታወቂያ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡


1. የማዕድ ቤት ቁሳቁሶች




ከብረት የተሰራ ድስት



ከብረት የተሰራ ማንቆርቆሪያ




የኤሌክትሪክ እንጀራ ምጣድ




ባሕላዊ የእንጀራ ምጣድ





ከሸክላ የተሰራ ጀበና



በጋዝ የሚሰራ ምድጃ







የሸክላ ድስት

በኤሌክትሪክ የሚሰራ ምድጃ


ሥዕል 2.12. ለምግብና ለመጠጥ ማዘጋጃ የሚያገለግሉ የማዕድ ቤት ቁሳቁሶች

2. የመመገቢያና የመጠጫ ቁሳቁሶች








ትሪ




ዝርግ ሣህን


መሶብ



ጭልፋ




ሹካ



ማንኪያ


ሥዕል 2.13 የመመገቢያ ቁሳቁሶች



ብርጭቆ



ኩባያ



ስኒ

ሥዕል 2.14. የመጠጫ ቁሳቁሶች

3. ለመቀመጫ ለመኝታ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች


ለመቀመጫ የምንጠቀምባቸው ቁሳቁሶች ምን ምን ናቸው? መኝታስ?

3. ለመቀመጫና ለመኝታ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች


ለመቀመጫ የምንጠቀምባቸው ቁሳቁሶች ምን ምን ናቸው? የመኝታስ?



በርጩማ



አልጋ




ወንበርና ጠረጴዛ


ሥዕል 2.15 የመቀመጫና የመኝታ ቁሳቁሶች

## 4. ቀላል የመገልገያ መሳሪያዎች


ሥዕሉን ከጥቅሙ ጋር አገናዝቡ።




መዶሻ




መጥረቢያ




ዶማ



መቀስ



ማጭድ




አካፋ

1. ለመቆፈሪያ የሚያገለግለው _______ ነው።
2. _______ አፈር ለመዛቅ ያገለግላል።
3. እንጨት ለመፍለጥ የሚያገለግለው ___________ ነው።
4. _________ ወረቀት ለመቁረጥ ያገለግላል።
5. _________ ምስመር ለመምታት ያገለግላል።
6. _________ ሳር ለመጨድ ያገለግላል።

ሥዕል 2.16 ቀላል የቤት መገልገያ ቁሳቁሶች

5. ለመዝናኛና ማስታወቂያ የሚያገለግሉ



ሥዕል 2.17 ለመዝናኛነትና ለማስታወቂያነት የሚጠቅሙ ቁሳቁስ

**በቤት ውስጥ የሚደረጉ ጥንቃቄዎች**

ልጆች! ስለታምና ሹል እቃዎች አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ?


ስለታምና ሹል የሆኑ የቤት ውስጥ የመገልገያ ዕቃዎች ቢላዋ፣ መቀስ፣ መጥረቢያ፣ ማጭድ፣ መርፌ፣ ወስፌና የመሳሰሉትን ስንጠቀም ስለቶቻቸው እንዳይቆርጡንና ሹልነታቸው እንዳይወጋን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡

በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የቤት ውስጥ የመገልገያ ዕቃዎችን በጥንቃቄ ካልተጠቀምን በሕይወታችን ላይ አደጋ ያደርሳሉ፡፡


የምግብ ማብሰያ የጋዝ ምድጃን፤ የከሰል እሳት ማንደጃዎችንና የመሳሰሉትን ስንጠቀም ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል፡፡

### 2.3.3. የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች መስሪያ


ልጆች! በቤታችሁ ውስጥ ያሉት የመገልገያ እቃዎች ከምን ከምን እንደተሰሩ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡





ቢለዋ ከምን ይሰራል?




የመመገቢያ ሹካና ማንኪያ ከምን ይሰራሉ?




ጠረጴዛና ወንበር ከምን ይሰራል?




የመመገቢያ ሳህን ከምን ከምን ይሰራል?



የመጠጫ ዕቃዎች ከምን ከምን ይሰራሉ?



የውሃ መቅጃ ባልዲ ከምን ከምን ይሰራል?




የልብስ ማጠቢያ ከምን ይሰራል?

ሥዕል 2.18 የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች የተሰሩባቸው ነገሮች፡፡

የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ተፈጥሮአቸው የተለያየ ነው፡፡

የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ለመስራት ከምንጠቀምባቸው የተለያዩ ነገሮች ውስጥ እንጨት፣ ብረት፣ ፕላስቲክና የመሳሰሉት ይገኛሉ፡፡





ሥዕል 2.19 ቀላል የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች የተሰሩባቸው ነገሮች

### 2.3.4. የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች አያያዝ

የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች አያያዝ ማለት ምን ማለትነው ?

የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን በንፅሕና መያዝ ጥቅሙ ምንድነው ?

የመመገቢያና የመጠጫ  እቃዎች ንፁህ መሆን አለባቸው፡፡  በንጽሕና ያልተያዘ የመመገቢያና የመጠጫ ዕቃ በሽታ ያመጣል፡፡



ሥዕል 2.20 በንፅሕና የተያዙ የቤት ቁሳቁሶች




ሥዕል 2.21 በአግባቡ የተያዙ የቤት ቁሳቁሶች

የቤት ውስጥ የመገልገያ እቃዎችን መወርወር አያስፈልግም፡፡ ሲቆሽሽ ማጠብና መጥረግ ያስፈልጋል፡፡

የቆሸሸ እቃ ካልተጠበ ምን ያስከትላል?

**ለቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች የሚደረግ ጥንቃቄ**

በቤት ውስጥ እቃ ተሰብሮባችሁ ያውቃልን? ከተሰበረባችሁ ችግሩ በምን እንደተቃለለ ለመምህራችሁ ንገሩዋቸው፡፡



ሥእል 2.22 ጥንቃቄ የጐደለው የቤት ቁሳቁስ አያያዝ

የቤት ውስጥ መገልገያ የሆኑ ጠርሙስና ሸክላ እቃዎች ተሰባሪዎች በመሆናቸው የተለየ አያያዝና ጥንቃቄ ያስፈልጋቸዋል፡፡

የኤሌክትሪክ መገልገያ መሳሪያዎችን እርጥበት ባለው እጅ መንካት አደገኛ ነው፡፡ ከተጠቀሙ በኋላ አድርቆና ጠርጐ ገመዶቹ ሰዎችን ጠልፈው እንዳይጥሉ በመጠቅለል በተገቢው ቦታ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

**መልመጃ 2.3**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. በጥንቃቄ ያልተያዘ እቃይሰበራል፡፡
2. በንጽሕና ያልተያዘ እቃ በሽታያመጣል፡፡
3. እቃ ያለቦታው መቀመጥ አለበት፡፡
4. አልጋ የመኝታ ቁሳቁስ ነው፡፡
5. ብርጭቆ እንጀራ ለመብያነት የሚያገለግል ቁሳቁስ ነው፡፡
6. ጠርሙስና ሸክላ ተሰባሪ አይደሉም፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

7. ከሚከተሉት ውስጥ ለመጠጫ የሚያገለግል ቁሳቁስ የቱ ነው?

ሀ/ ኩባያ ለ/ ሹካ ሐ/ ሳህን

8. ወጥ ለማውጫ የምንጠቀምበት እቃ ምን ይባላል?

ሀ/ ምጣድ ለ/ ጭልፋ ሐ/ ሹካ

9. ከሚከተሉት ቁሳቁሶች ውስጥ አንዱ ለመመገቢያነት የሚያገግል ነው፡፡

ሀ/ ትራስ ለ/ ወንበር ሐ/ ሳህን

10.ለጓሮ አትክልት አንክብካቤ የምንጠቀምበት ቁሳቁስ የቱ ነው?

ሀ/ መዶሻ ለ/ መኮትኮቻ ሐ/ ምስማር

**ማጠቃለያ**

- የቤተሰብ አባላት የምንላቸው ወላጆች /እናትና አባት/፣ ወንድሞች፣ እህቶች፣ አጐቶች፣ አክስቶችና አያቶች ናቸው፡፡
- የቤተሰብ አባላት ከሚሰሩዋቸው የስራ አይነት ውስጥ ግብርና፣ ንግድ፣ ውትድርና ፣ ሙያተኛ፣ የቢሮ ሥራ፣የቀን ስራ ተጠቃሾች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
- የልጆች የሥራ ድርሻ መማር ፣ የቤተሰብን ደንብ ማክበር፣ መታዘዝ፣ ቤተሰብን በአቅም መርዳት ናቸው፡፡
- ቤተሰባዊ መልካም ግንነት የምንላቸው መተሳሰብ፣ መግባባት፣ መፈቃቀር፣ መከባበር፣ በስራ መረዳዳት፣ ችግርን በጋራ መፍታትና ታማኝነትናቸው፡፡
- ግብርና በአካባቢያችን ዋና የምግብ ምንጭ ነው፡፡ ግብርና ስንል የእንስሳት እርባታና የእርሻ ሥራን ያጠቃልላል፡፡
- ልዩ ልዩ የልብስ አይነቶች ከተለያዩ ግብአቶች ይሰራሉ፡፡ እነዚህም፡- ከጥጥ፣ ከሱፍ፣ ከቆዳና ከናይለን ናቸው፡፡
- መጠለያ የአንድ ቤተሰብ መሰረተዊ ፍላጐት ነው፡፡ መጠለያ የምንላቸው ጐጆ ቤት፤ ቆርቆሮ ቤት፤ አፓርታማ ቤቶች ናቸው፡፡
- የቤት ቁሳቁስ አይነቶች የኤሌክትሪክ እቃዎች፣ ከሸክላ የተሰሩ እቃዎች፣ ከእንጨት የተሰሩ እቃዎች፣ ከብረት የተሠሩ እቃዎችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችየምንላቸው ለምግብነትና ለመጠጥ ማዘጋ□ነት፣ ለመመገቢያና ለመጠጫ፣ ለመቀመጫና ለመኝታ፣ ለመዝናኛና ለማስታወቂያ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

የቤተሰብ አባላት የምንላቸው እናትና አባት ብቻ ናቸው፡፡

1. ልጅ የቤተሰብ አባል አይደለም፡፡
2. ከልጆች የሥራ ድርሻ አንዱ መማር ነው፡፡
3. በቤት ውስጥ ሴት ልጅና ወንድ ልጅ እኩል የሥራ ድርሻ አላቸው፡፡
4. በቆሎ የግብርና ውጤት ነው፡፡

**ለ/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከ "ለ" ስር የተሰጡትን ከ"ሀ" ስር ከተሰጡት ጋርበማዛመድ መልሱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 6. ለመጠጫነት ያለግላል | ሀ. ቢለዋ |
| 7. ለወጥ መስሪያ ያለግላል | ለ. ምጣድ |
| 8. ሽንኩርት ለመክተፍ ያገለግላል | ሐ. ጀበና |
| 9. እንጀራ ለመጋገር ይጠቅማል | መ. ብረትድስት |
| 10. ቡና ለማፍላት ያገለግላል | ሠ. ኩባያ |
| | ረ. ወንበር |

**ሐ/ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ስጡ፡፡**

11. ለመጠጫነት ከሚያለግሉ ቁሳቁሶች ሦስቱን ጻፉ፡፡
12. የወላጆች የሥራ ድርሻ የሆኑትን ጥቀሱ፡፡
13. የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁስ የምንላቸው ምን ምን ናቸው?


# ክፍል ትምህርት ሦስት

## 3. ትምህርት ቤታችን

### 3.1. የትምህርት ቤታችን ግቢ

| መታወቅ የሚባቸው ቃላት | |
|---|---|
| - አቅጣጫ | - ሰንደቅ አላማ |
| - ፀጥታ | - ማበለፀጊያ |
| - ጥቁር ሰሌዳ | - ማእከል |
| - አክብሮት | - ቤተሙከራ |
| - እርስ በርስ | |

ተማሪዎች! በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ምን ምን ነገሮች ይገኛሉ?



ስእል 3.1. የትምህርት ቤት ግቢ

### 3.1.1. የትምህርት ቤት ግቢ የያዛቸው ልዩ ልዩ ቦታዎች


ትምህርት ቤታችሁ ከቤታችሁ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?

የትምህርት ቤታችሁን መጠሪያ ሙሉ ስም ማን ይባላል?

ትምህርት ቤታችሁ ከቤታችሁ በየትኛው አቅጣጫ እንደሚኝ ለማወቅ በመጀመሪያ አራት ዋና ዋና አቅጣጫዎችን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም አቅጣጫዎች ፡-

- ሰሜን
- ደቡብ
- ምእራብና
- ምስራቅ ይባላሉ፡፡

ከዚህም በመነሳት የትምህርት ቤታችሁን አቅጣጫ ከቤታችሁ በየትኛው በኩል እንደሆነ መለየት ትችላላችሁ፡፡ በተጨማሪም የሚከተለውን ስእል ተመልከቱ፡፡



ሥእል 3.2 ቦታዎችን በአቅጣጫ መለየት

ዛፉ ከልጁ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?

ትምህርት ቤቱ ከልጁ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?


በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በአብዛኛው የሚገኙ ቦታዎች፡-

- የስፖርት ሜዳ
- የአስተዳደር ሕንፃ
- የመማሪያ ክፍሎች
- ሰንደቅ አላማ
- የጥበቃ ቤት
- የሽንት ቤት
- ቤተመጽሐፍ
- ቤተሙከራ
- የትምህርት ማበልፀጊያ ማእከል
- የመምህራን መሰብሰቢያና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ቤተ መጽሐፍ ገብታችሁ ታውቃላችሁ?

ቤተ መጽሐፍ የምንለው ብዙ አይነት መጻሕፍት የሚገኙበት ሥፍራ ነው፡፡







ሥእል 3.3. በትምህርት ቤት የሚገኝ ቤተ መጽሐፍ

## የቤተ-መጽሐፍ አጠቃቀም

ቤተ መጽሐፍ ውስጥ ገብታችሁ ስትጠቀሙ ማድረግ የሚገባችሁ ጥንቃቄ፡-

- በፀጥታ ማንበብ /ድምጽን አለማሰማት/
- መጽሐፉን በጥንቃቄ መያዝ /አለመቅደድ፣ በመጽሐፉ ላይ አለመጻፍ/






ሥእል 3.4. የሽንት ቤት አጠቀቀም

- ስትጨርሱ በተገቢው ቦታ መመለስ

ሥእል 3.4. የሽንት ቤት አጠቀቀም

ሽንት ቤት ስትጠቀሙ በተሰራው ጉድጓድ ውሰጥ መጠቀምና ከተጠቀማችሁም በኋላ ጉድጓዱን መክደን ያስፈልጋል፡፡ ከሽንት ቤት ተፀዳድታችሁ ከወጣችሁ በኋላ እጃችሁን በውሃና በሳሙና መታጠብ ተገቢ ነው፡፡ እንደሁም ምግብ ከመመገባችሁ በፊት እጃችሁን በሚገባ መታጠብ ያስፈልጋል፡፡

ልጆች! በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ምን ምን ናቸው?




ሥእል 3.5. በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ነገሮች

ከስእሉ ምን ተመለከታችሁ?

በክፍላችሁ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ፡-

- የተማሪ መቀመጫ
- የመምህርመቀመጫና ወንበር
- ጥቁር ሰሌዳና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የእያንዳንዳቸውን ጥቅም ምን ምን እንደሆነ ተናገሩ፡፡

### 3.1.2. በትምህርት ቤት የሚከናወኑ ተግባራት

በትምህርት ቤት ውስጥ የሚናወኑ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች አሉ፡፡ እነሱም

- መማር
- ማስተማር
- ልዩ ልዩ ስፖርታዊ ጨዋታዎች
- ልዩ ልዩ የክበባት እንቅስቃሴዎችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### 3.1.3. በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎች መልካም ግንኙነት

ከመምህራኖቻችሁና ከጓደኞቻችሁ ጋር ምን አይነት ግንኙነት አላችሁ?
ልጆች! ከጓደኞቻችሁ ጋር ስትጫወቱ ትግባባላችሁን?




ሥእል 3.6. የእርስ በእርስ መልካም ግንኙነት



ሥዕል 3.7 ተማሪው ለመምህሩ በአክብሮት ሰላምታ ሲሰጥ

ሰዎች በሕብረት ሲኖሩ መግባባት አለባቸው፡፡ እናንተም ከጓደኞቻችሁ ጋር ስትጫወቱም ሆነ ስትነጋገሩ መግባባት አለባችሁ ፡፡ መደማመጥ ከሌለ መግባባት ስለማይኖር አንዱ የሚናገረውን ሌላው ማዳመጥ ይኖርበታል፡፡

**መልመጃ 3.1.**

ሀ/ ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. የትምህርት ቤታችሁን መምህራንና ሰራተኞች ማክበር ይገባችኋል፡፡
2. በተማሪዎች መካከል መልካም ግንኙነት መኖር ጥቅም የለውም፡፡
3. በትምህርት ሰዓት መጫወት ተገቢ ነው፡፡

ለ/ ከተሰጡት አማራጮች መከከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

4. በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኘው የቱ ነው?

   ሀ/ ጥቁር ሰሌዳ ለ/ የመጫወቻ ሜዳ ሐ/ ሽንት ቤት

5. ከቤተ መጽሐፍ አጠቃቀም ውስጥ አንዱ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ/ በፀጥታ ማንበብ ለ/ መጽሐፍ መቅደድ ሐ/ ሲያነቡ መጮህ

6. በትምህርት ቤት ውስጥ ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ አንዱ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ/ መማር ለ/ ማስተማር ሐ/ ሁሉም መልስ ነው፡፡

## 3.2.የትምህርት ቤት ሕግና መመሪያ ማክበር

### 3.2.1. የትምህርት ቤት መመሪያ

| መታወቅ የሚባቸው ቃላት |
|---|
| - የደንብ ልብስ<br>- ንብረት<br>- ቅጥር ግቢ<br>- እንክብካቤ<br>- ሕግና ደንብ<br>- ጥሞና |

ልጆች! የትምህርት ቤታችሁን ሕግና ደንብ ታውቃላችሁ?


የትምህርት ቤት ደንብና ሥነ-ስርአት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡ ይኸውም፡-

- የትምህርት መሳሪያዎችን አሟልቶ በአግባቡ መያዝ፣
- የትምህርት ሰአትን አክብሮ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት፣
- የትምህርት ቤት ደንብ ልብስ /ዩኒፎርም/ በመልበስ ወደ ትምህርት ቤት መሄድ፣
- በትምህርት ሰአት ክፍል ውስጥ ቁጭ ብሎ በጥሞና መማር፣
- በእረፍት ሰአት መጫወት፣
- በክፍል ውስጥ አለመረበሽ፣
- ያለምክንያት ከትምህርት ቤት አለመቅረት፣
- የትምህርት ቤትን ንብረት መጠበቅ፣
- መምህራንን ማክበር፣
- የሚሰጡ ሃላፊነቶችን መወጣትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡



ሥእል 3.8. በእረፍት ሰአት ልጆች ሲጫወቱ

ልጆች! የትምህርት ቤት ንብረትን እንዴት እንከባከባለን?




ሥእል 3.9 ተማሪዎች አበቦችንና አትክልቶችን ውሃ ሲያጠጡ

ከስእሉ ምን ተረዳችሁ? እናንተስ እንደነዚህ ልጆች አትክልቶችን ትንከባከባላችሁ?

በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢና በክፍል ውስጥ የተለያዩ ንብረቶች ይገኛሉ፡፡ የራሳችሁን፣ የጓደኞቻችሁንና የትምህርት ቤታችሁን ንብረቶች ለይታችሁ ማወቅ፣ መንከባከብና በአግባቡ መጠቀም ይገባችኋል፡፡

ልጆች! እስቲ የራሳችሁንና የጓደኞቻችሁን ንብረቶች ለይተችሁ ዘርዝሩ፡፡

ከዚህ በታች የቀረበውን ሰንጠረዥ በምሳሌዎቹ እንደተመለከቱት በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ ለሚገኙ የትምህርት ቤቶችና የግል ንብረቶቻችሁ የምታደርጉትን እንክብካቤ /ጥንቃቄ / ሙሉ፡፡

| ተ/ቁ | የንብረት አይነት | የሚደግለት እንክብካቤ |
|---|---|---|
| 1 | ወንበሮች ፤ ጠረጴዛዎች | እንዳይሰበሩ ጥንቃቄ ማድረግ |
| 2 | ደብተሮች፣ መጻሕፍት፣ እስክሪፕቶ… | እንዳይቀደዱና እንዳይጠፉ መጠንቀቅ |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |
| 6 | | |
| 7 | | |
| 8 | | |

ሰንጠረዥ 3.1. ለንብረት የሚደረግ እንክብካቤ /ጥንቃቄ/

**መልመጃ** 3.2.

**ሀ/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. መምህር ሲያስተምር በክፍል ውስጥ አለመረበሽ ጥሩ ሥነ-ምግባር ነው፡፡
2. በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ አበቦችንና አትክልቶችን መንከባከብ ያስፈልጋል፡፡
3. በትምህርት ቤት የሚገኙ ንብረቶችን መስበር አለብን፡፡

**ለ/ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡**

4. ወደትምህርት ቤት ስትሄዱ ማድረግ ያለባችሁ ምንድነው?

   ሀ/ ሰአት አክብሮ መሄድ

   ለ/ የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ /ዩኒፎርም/ መልበስ

   ሐ/ ሁሉም ልክ ናቸው፡፡

5. ከሚከተሉት አንዱ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ይገኛል፡፡

   ሀ/ ወንበር ለ/ መማሪያ ክፍል ሐ/ ሁሉም

## 3.3. ጥሩ /መልካም/ የሆኑ የግል ግንኙነቶች

| |
|---|
| **መታወቅ የሚገባቸው ቃላት**<br>- መላላክ<br>- የግል<br>- ጉርብትና<br>- በጋራ<br>- ጾታ |


### 3.3.1. በቤትና በጐረቤት ያለ መልካም ግንኙነት

ተማሪዎች! ከትምህርት ቤት መልስ ምን ታደርጋላችሁ?

ጊዜያችሁን በአግባቡ ትጠቀማላችሁ?

አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት ከተመለሰ በኋላ ማድረግ የሚባው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ለወላጆች መላላክ
- ወላጆችን በስራ ማገዝ
- ጠንክሮ ማጥናት
- በትርፍ ጊዜ መጫወት
- መታዘዝ



ስእል 3.10 ልጆች ጊዜያቸውን በአግባቡ ሲጠቀሙ

ልጆች ከጐረቤቶቻችሁ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ምን ይመስላል?
የመልካም ጉርብትና መገለጫዎች የምንላቸው፡-

- በጋራ መስራት እና መረዳዳት፣
- መከባበር፣
- በጾታ እና በሃይማኖት እኩልነት ማመን፣
- አብሮ ችግርን እና ደስታን መካፈል፣
- የታመመን መጠየቅና የመሳሰሉት ናቸው፡፡



ስእል 3.11 ጐረቤታሞች ቡና እየጠጡ ሲወያዩ



ስእል 3.12 አካባቢን በጋራ ማልማት

**መልመጃ 3.3**

**ሀ/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን “ሀሰት” በማለት መልሱ፡፡**

1. ልጆች ከትምህርት ቤት መልስ ለወላጆቻችሁ መላላክ አለባቸው፡፡
2. ልጆች ከትምህርት ቤት መልስ ጊዜያቸውን በአግባቡ መጠቀም አለባቸው፡፡
3. ከጐረቤት ጋር መልካም ግንኙነት አያስፈልግም፡፡

**ለ/ ከተሰጡት አማራጮች መሀከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

4. ከሚከተሉት አንዱ የመልካም ጉርብትና መገለጫ ነው፡፡

   ሀ/ መከባበር ለ/ መጨቃጨቅ ሐ/ አለመግባባት

5. ጥሩ ጐረቤት የሚባለው

   ሀ/ የሚረዳዳ ለ/ ችግርንና ደስታን የሚካፈል ሐ/ ሁሉም


### 3.4. የመንገድ ላይ ጥንቃቄ


| መታወቅ የሚባቸው ቃላት |
|---|
| - ድልድይ |
| - አዛውንት |
| - አካል ጉዳተኛ |
| - ቅደም ተከተል |
| - ዥርንጉርጉር መስመር |

#### 3.4.1 የመንገድ ላይ አደጋዎች

የመኪና መንገድ ለማቋረጥ ሲፈለግ መደረግ የሚባው ጥንቃቄ ተናገሩ፡፡
ከቤት ወደ ትምህርት ቤት ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ስትሄዱም ሆነ ስትመለሱ ማድረግ የሚገባችሁ ጥንቃቄዎች፡-

- በመንገዱ በግራ በኩል ብቻ መጓዝ
- ለሰው በተፈቀደው ዥርንጉርጉር /ዜብራ/ ምልክት ማቋረጥ
- በመኪና መንገድ ላይ አለመጫወት






ሥእል 3.13 የመንገድ ላይ ጥንቃቄዎች

ሰዎች መንገድ ሲያቋርጡ ጥንቃቄ ካላደረጉ አደጋ ሊደርስባቸው ይችላል፡፡

በመኪና መንገድ ላይ መጫወት አደጋ ያመጣል፡፡



ስእል 3.14 ጥንቃቄ የጐደለው የመንገድ አጠቃቀም

### 3.4.2. የመንገድ ላይ አደጋዎችን መከላከል

የመንገድ ላይ አደጋ መከላከያ ጥንቃቄዎች

የመንገድ ላይ አደጋዎችን ለመቀነስ፡-

- በመኪና መንገድ ላይ ንቃት ባለው ሁኔታ መጓዝ፣
- ቀኝና ግራን ተመልክቶ ማቋረጥ፣

- ድልድዮችን፣ መረማመጃዎችንና የሚያዳልጡ ቦታዎችን በጥንቃቄ ማለፍ፣
- በመንገድ ላይና በመንገድ ዳር አለመጫወት፣
- የመንገድ ላይ ማቋረጫ መስመሮችን በጥንቃቄና በአግባቡ መጠቀም፡፡

መኪና መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ ሌሎችን ማለትም

- ሕፃናትን
- አዛውንትንና
- አካል ጉዳተኞችን መርዳት ያስፈልጋል፡፡

**መልመጃ 3.4.**

**ሀ/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. በመኪና መንገድ ላይ መጫወት አደጋ ያስከትላል፡፡
2. ሁልጊዜ በግራ በኩል ብቻ መጓዝ አያስፈልግም፡፡

**ለ/ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

3. ከሚከተሉት አንዱ መኪና መንገድ ለማቋረጥ የሚያስፈልገን ጥንቃቄ ነው፡፡

   ሀ. ግራና ቀኝን ተመልክቶ ማቋረጥ

   ለ. በኾንጉርጉር ምልክት ማቋረጥ

   ሐ. ሁሉም መልስ ነው፡፡

4. መኪና መንገድ ስናቋርጥ መርዳት ከሚባን ሰዎች መካከል፤

   ሀ. አዛውንቶችን ለ. አካል ጉዳተኞችን ሐ. ሁሉም

5. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የመኪና አደጋ የማያስከትል ነው፡፡

   ሀ. መኪና መንገድ ላይ መጫወት

   ለ. በኾንጉርጉር /ዜብራ/ ማቋረጫ ማለፍ

   ሐ. ቀኝና ግራን ሳያዩ ማቋረጥ

### 3.5. በትምህርት ቤታችን የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች

መታወቅ የሚባቸው ቃላት

- ጠርዝ
- ትርፍ
- ጐን
- ቅርጽ

#### 3.5.1. ወረቀት በመጠቀም የተለያዩ ቅርፃ ቅርጾችን መስራት

ተማሪዎች! ወረቀት፣ ካርቶንና ሌሎችን ነገሮች በመጠቀም የተለያዩ ቅርፃ ቅርጽ ያላቸውን መጫወቻዎች መስራት ይቻላል፡፡

በዚህ መሰረት ቀጥሎ በተሰጡት ቅደም ተከተሎች በመጠቀም ተግባራዊ መጫወቻዎችን ስሩ፡፡


**ተግባራዊ ክንዋኔ 3.1.**

መከተል የሚባን ቅደም ተከተሎች


1. ንፁህ ወረቀት ማዘጋጀት




2. ወረቀቱን በሁሉም ጐን እኩል እንዲሆን ትርፍ የሆነውን ወረቀት መቁረጥ




3. እኩል ጐን ያለውን ወረቀት መሃከል ለማግኘት ከቀኝ ጫፍ ወደ ግራ ማጠፍ በድጋሚ ከግራ ጫፍ ወደ ቀኝ ማጠፍ፤ በመጨረሻም እኩል ጐን ያለውን ወረቀት መሀከል ማግኘት





4. ቀጥሎ እያንዳንዱን ጠርዝ ጫፍ ወደ መሀል ማጠፍ





5. በቅደም ተከተል 4 መ ላይ የሚገኘውን በመገልበጥ እንደገና በወረቀት ጀርባ የሚገኘውን የወረቀት መሀል በማግኘት እያንዳንዱን ጫፍ በድጋሚ ወደ መሃል ማጠፍ፤




6. በእያንዳንዱ ሦስት ጐን ቅርጽ ላይ ከ1 እስከ 8 ቁጥሮችን መጻፍ። በተጨማሪ እያንዳንዱን ጠርዝ በሚገባ ማጠፍ።



7. ቁጥር በተፃፈበት በስተጀርባ /ወረቀቱን በመገልበጥ/ በተለያዩ ቀለሞች በአራቱም ገጽታ ላይ ምልክት ማድረግና የቀለሞቹን ስም መፃፍ።



8. በመጨረሻ ሁለቱን የአውራ ጣቶችና ሁለቱን አመልካች ጣቶች በወረቀቱ ላይ ባሉት አራት ኪሶች በማስገባት በጣቶቻችን ወረቀቱን መግፋት።



ከዚህ በተጨማሪ ሳጥኖችን፣ በነፋስ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን በወረቀት እና በሌሎች ቁሳቁሶች መስራት ይቻላል።

**ማ ጠ ቃ ለ ያ**

- አንድን ቦታ ለይቶ በአቅጣጫ ማወቅ ይቻላል፡፡ አቅጣጫዎች የምንላቸው ሰሜን፤ ደቡብ፤ ምእራብና ምስራቅ ይባላሉ፡፡
- የትምህርት ቤት ግቢ የያዛቸው ልዩ ልዩ ቦታዎች የስፓርት ሜዳ፣ የአስተዳደር ሕንፃ፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ የሰንደቅ አላማ፣ የጥበቃ ቤት፣ የሽንት ቤት፣ ቤተ መጽሐፍ፣ ቤተ ሙከራ፣ የትምህርት ማበልፀጊያ ማእከል፣ የመምህራን መሰብሰቢያ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- በትምህርት ቤት ውስጥ የሚናወኑ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች መማር፣ ማስተማር፣ ልዩ ልዩ ስፖርታዊ ጨዋታዎች፣ በተለያዩ ክበባት መሣተፍ፣ ወዘተ.
- በትምህርት ቤት ውስጥ መልካም ግንኙነት የሚኖረው በመግባባት፣ በመደማመጥ፣ በሕብረት በመስራት ነው፡፡
- የትምህርት ቤት ደንብና ሥነ-ሥርአቶች ሲባል የትምህርት መሳሪያዎችን አሟልቶ በአግባቡ መያዝ፣ ሰአትን አክብሮ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት፣ የደንብ ልብስ መልበስ፣ አለመረበሽ፣ ያለምክንያት ከትምህርት ቤት አለመቅረት፣ የትምህርት ቤቱን ንብረት መጠበቅ ናቸው፡፡
- መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ልጅ ከትምህርት ቤት መልስ ለወላጆች መላላክ፣ ወላጆችን በስራ ማገዝ፣ ጠንክሮ ማጥናት፣ በትርፍ ጊዜ መጫወትና መታዘዝ ያከናውናሉ፡፡
- በተጨማሪም የመልካም ጉርብትና መገለጫዎች የምንላቸው በጋራ መስራትና መረዳዳት፣ መከባበር፣ በጾታና በሃይማኖት እኩልነት ማመን፣ አብሮ ችግርና ደስታን መካፈልና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- በመንገድ ላይ የመኪና አደጋ እንዳይደርስብን ማድረግ የሚገቡን ጥንቃቄዎች በመንገዱ በግራ በኩል ብቻ መጓዝ፣ ለሰው በተፈቀደው ማቋረጫ ዥንጉርጉር መንገድ ላይ መሄድ፣ በመኪና መንገድ ላይ ያለመጫወት ናቸው፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. ሰላምታ መለዋወጥ የመልካም ግንኙነት ምልክት ነው፡፡
2. የትምህርት ሰአት አክብሮ መገኘት የስንፍና ምልክት ነው፡፡
3. ሽንት ቤት ከተፀዳዳን በኋላ እጃችንን ባንታጠብ ችግር አያመጣብንም፡፡
4. ክፍል ውስጥ ወንበር ላይ ወጥቶ መቆም የጐበዝ ተማሪ ምልክት ነው፡፡
5. ተማሪዎች በውይይት ጊዜ ከተደማመጡ አይግባቡም፡፡

**ለ. የሚከተሉትን በ"ሀ" ስር የሚገኙትን ጥያቄዎች ከ "ለ" ስር ከሚገኙት ጋር አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 6. ጥቁር ሠሌዳና የተማሪ መቀመጫ ይገኝበታል | ሀ. ሽንት ቤት |
| 7. ብዙ አይነት መጽሐፍ የሚገኝበት ሥፍራ | ለ. የመማሪያ ክፍል |
| 8. ትምህርት ቤት ውስጥ የሚከናወን ተግባር | ሐ. ቤተ መጽሐፍ |
| 9. ንጽሕናው በሚገባ መጠበቅ አለበት | መ. በክበባት መሳተፍ |
| | ሠ. ቤተሙከራ |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

10. የጐረቤት ልጆች ምን ማድረግ አለባቸው?

ሀ/ መጣላት ለ/ አብሮ መጫወት ሐ/ መረበሽ

11. መልካም የሆነ የጉርብትና ሥነ ምግባር የቱ ነው?

ሀ/ አካባቢን ማቆሸሽ ለ/ ጐረቤትን በጩኸት መረበሽ

ሐ/ የታመመን መጠየቅ

12. የመንገድ ላይ አደጋዎችን ለመቀነስ ማድረግ ያለብን

ሀ/ በመንገድ ስንሄድ ንቃት ባለው ሁኔታ መጓዝ

ለ/ እግረኛ ማቋረጫ መስመሮችን በጥንቃቄና በአግባቡ መጠቀም

ሐ/ ሁሉም

# ክፍለ ትምህርት አራት

## 4. መንደራችን ቀበሌያችን


### 4.1. የቀበሌያችን መገኛ

**መታወቅ የሚገባቸው ቃላት**

- ቀበሌ
- ገጠር
- ደን
- የፀሐይ መውጫ
- የፀሐይ መግቢያ

ልጆች! ያላችሁበትንወይም የምትኖሩበትን ቀበሌ ስም ማን በመባል ይታወቃል?

እናንተ ቀበሌ ውስጥ ምን ምን ነገሮች ይገኛሉ?




ሥዕል 4.1. በቀበሌ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች

በሥዕሉ ላይ ምን ተመለከታችሁ?

በእናንተ ቀበሌ ውስጥ የሚገኙ የትኞቹ ናቸው?

የምትኖሩበት ቀበሌ የገጠር ከሆነ የገጠር ቀበሌ ይባላል፡፡ የከተማ ከሆነ ደግሞ የከተማ ቀበሌ ይባላል፡፡

የነአበበች መኖሪያ ቤት ከቀበሌያቸው በቀኝ በኩል ይገኛል፡፡ አበበች ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ወደ ትምህርት ቤት በቀበሌው ፊት ለፊት ባለው ትልቁ መንገድ ትሄዳለች፡፡ የነአበበች ትምህርት ቤት የሚገኘው ከቀበሌያቸው ራቅ ብሎ በስተግራ በኩል ነው፡፡ ከቀበሌው በስተኋላ ጥቅጥቅ ያለ ደን ይገኛል፡፡





ሥእል 4.2. አንፃራዊ መገኛ

የምትኖሩበት ቀበሌ ከመኖሪያ ቤታችሁ እና ከምትማሩበት ትምህርት ቤት በየት በኩል ይገኛል?

### 4.1.1 አቅጣጫን መናገር

ቀጥሎ ያለውን ሥዕል በመመልከት አቅጣጫን በመለየት ለክፍል ጓደኞቻቸው ተናገሩ፡፡



ሥዕል 4.3. አቅጣጫን መለየት

ልጆች! ፀሐይ የምትወጣበትን አቅጣጫ አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? የምትጠልቅበትንስ?

በሥዕል 4.3 እንደሚታየው ፊታችሁን ወደ ፀሐይ መውጫ መልሱና እጃችሁን ወደ ግራና ወደ ቀኝ ዘርግታችሁ ቁሙ፡፡ ከአቋቋማችሁ አኳያም ከፊት ለፊታችሁ ያለው አቅጣጫ ወይም የፀሐይ መውጫ ምስራቅ ሲባል በጀርባችሁ በኩል ያለው ደግሞ ፀሐይ የምትጠልቅበት ምዕራብ ይባላል፡፡ እንዲሁም የግራ እጃችሁ አቅጣጫ ሰሜን ሲሆን ፤ የቀኝ እጃችሁ አቅጣጫ ደግሞ ደቡብ ይባላል፡፡

**መልመጃ 4.1.**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1 ፊታችሁን ወደ ፀሐይ መጥለቂያ መልሳችሁ ብትቆሙ በጀርባችሁ ያለው አቅጣጫ ምን ይባላል?

ሀ/ ደቡብ ለ/ ሰሜን ሐ/ ምስራቅ

2 ፊታችንን ወደ ፀሐይ መውጫ ብናደርግ የቀኝ እጃችን የትኛውን አቅጣጫ ያመለክታል?

ሀ/ ሰሜን ለ/ ደቡብ ሐ/ ምስራቅ


3. ፀሐይ በየትኛው አቅጣጫ ትወጣለች?

ሀ/ በምዕራብ ለ/ በሰሜን ሐ/ በምስራቅ


## 4.2. በአካባቢያችን የሚገኙ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች

| መታወቅ የሚገባቸው ቃላት | |
|---|---|
| - ክንዋኔ | - መንከባከብ |
| - ሲባጎ | - አግድም ማረስ |
| - የተፈጥሮ ሀብት | |
| - ቅርፅ | |
| - ደቃቅ | |
| - ሽክላ አፈር | |
| - ዳለቻ | |


በአካባቢያችሁ ሕይወት የሌላቸው ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡




ድንጋይ




አፈር




ውሃ



ወንበር ጠረጴዛ



መኪና



የመጠጫና የመብያ ዕቃ

ሥዕል 4.4. ሕይወት የሌላቸው ነገሮች


ሕይወት የሌላቸው ነገሮች በምን ይታወቃሉ?

ሕይወት የሌላቸው ነገሮች የተፈጥሮ ሀብት ናቸው፡፡ እነዚህም አፈር፣ ድንጋይ፣ የር፣ ውሃና የመሳሰሉት ናቸው

**ሕይወት የሌላቸው ነገሮችና ባሕሪያቸው**

1. ሕይወት የሌላቸው ነገሮች አይመገቡም፡፡


ለምሳሌ ፡-



ብርጭቆ ሣህን ቢላዋ


ሥዕል 4.5. ሕይወት የሌላቸው ነገሮች አይመገቡም፡፡

2. ሕይወት የሌላቸው ነገሮች አይተነፍሱም፡፡



ሬዲዮ መጽሐፍ


ሥዕል 4.6. ሕይወት የሌላቸው ነገሮች አይተነፍሱም፡፡



ጠረጴዛ



ሳሙና




ብረት




እንስራ

ሥእል 4.7. ሕይወት የሌላቸው ነገሮች አያድጉም፡፡

4. ሕይወት የሌላቸው ነገሮች በራሳቸው አይንቀሳቀሱም፡፡



መኪና



ሳይክል

ሥዕል 4.8 ሕይወት የሌላቸው ነገሮች አይንቀሳቀሱም፡፡

ሕይወት የሌላቸው ነገሮች በሦስት ይመደባሉ፤ እነሱም፡-

ጠጣር ነገሮች

ፈሳሽ ነገሮች

ጋዞች /አየር/ ናቸው፡፡

**ተግባራዊ ክንዋኔ 4.1.**

በአካባቢያችሁ የሚገኙ ነገሮችን ሰብስቡ፡፡ እያንዳንዳቸውን በደንብ አስተውላችሁ ጠጣር ወይም ፈሳሽ በማለት መድባችሁ በአይነት ለዩዋቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ድንጋዮች | ዘይት |
| ብረታ ብረቶች | ወተት |
| ወረቀቶች | ኘላስቲክ |
| ውሀ | |
| አፈር | |
| ደረቅ እንጨት | |

እያንዳንዳቸውን በደንብ አስተዋላችሁ? በቀለም የሚመሳሰሉት የትኞቹ ናቸው? በክብደትስ? በቅርፅ የሚመሳሰሉስ አሉ? የትኞቹ ናቸው? ሁሉም በመጠን እኩል ናቸው? ወይስ ይበላለጣሉ?

## 4.2.1.አየር

የአየር መኖር

ልጆች! አየር በአይን የማይታይና በእጅ የማይዳሰስ በአካባቢያችን ያለ ነገር ነው፡፡ ነገርግን ዛፎችንሲያወዛውዝ እናያለን፡፡


የመኪና ጎማ በአየርካልተሞላ መኪናው መንቀሳቀስ አይችልም፡፡

አየር መኖሩን በዚህ ማወቅ እንችላለን፡፡


የአየር ጥቅም

አየር ሕይወት የለውም፡፡ ነገር ግን ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ይጠቀሙታል፡፡

እፅዋትና እንስሳት ያለ አየር መኖር አይችሉም፡፡



ሠዎች ይተነፍሳሉ



ለታመመ ሰው አየር ሲሰጠው



ኳስ ውስጥ አየር ሲሞላ



ባሉን አየር ተሞልቶ

ሥዕል 4.9 የአየር ጥቅም

**ተግባራዊ ክንዋኔ 4.2.**


**አስፈላጊ ነገሮች**

- በሁለት ጣሳዎች ውስጥ የበቀሉ አረንጓዴ ችግኞች
- አንድ ወፍራም ላስቲክ
- ጠረጴዛ
- ሲባጎ /ገመድ/

**አሠራር፡-**

በጣሳዎቹ ውስጥ ያሉትን ተክሎች ጠረጴዛ ላይ አስቀምጡ፡፡

ከሁለቱ አንዱን አየር በማያስገባ ወይም ቀዳዳ በሌለው ላስቲክ ሸፍናችሁ እሰሩት፡፡ ለጥቂት



ቀናት በዚህ አይነት ይቆዩ፡፡

ሥእል 4.10 እፅዋት አየር ያስፈልጋቸዋል፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላ በሁለቱ ተክሎች መካከል ያለውን ልዩነት በደንብ ተመልከቱ፡፡ ልዩነቱ ከምን መጣ? ተወያዩበት፡፡

እያንዳንዳችሁ ለጥቂት ሰከንዶች ብቻ አፍና አፍንጫችሁን እፍን አድርጉና ያዙ፡፡ ምን ተሰማችሁ? ለምን?

የአየር ንጽሕናን እንዴት መጠበቅ እንችላለን?

አየር በተለያዩ መንገዶች ሊበከል ይችላል፡፡ ለምሳሌ ፡-

- ቆሻሻን በየቦታው መጣልና ማቃጠል /ጐማ ፤ ፌስታል ወዘተ./
- ከመኪና ሞተሮችየሚወጣ ጭስ
- ከተለያዩ ፋብሪካዎች የሚወጣ ጭስና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የአካባቢያችንን የአየር ንጽሕና ለመጠበቅ


- ደረቅ ቆሻሻን በጉድጓድ ውስጥ አድርጐ ለእፅዋት ማዳበሪያነት መጠቀም
- አካባቢያችንን በአረንጓዴ ተክሎች ማልማት ወዘተ. ናቸው፡፡

### 4.2.2 ውሃ

በአካባቢያችሁ ውሃን ከየት ታገኛላችሁ?

የውሃ መገኛ

- ውሃ ከተፈጥሮ ሀብቶች አንዱ ነው፡፡
- የውሃ መገኛዎች ብዙ ናቸው፡፡ እነርሱም
    - ከቧንቧ
    - ከጉድጓድ
    - ከኩሬ
    - ከምንጭ
    - ከወንዝና
    - ከዝናብ ናቸው፡፡



ሥዕል 4.11 የውሃ መገኛዎች

በአካባቢያችሁ እናንተ የምትጠጡት ውሃ የሚገኘው ከየትኛው ነው?

ለበሽታ የማያጋልጠው ንፁህ ውሃ ከየት ይገኛል?

አብዛኛውን ጊዜ ንፁህ ውሃ የምናገኘው ከቧንቧ፣ በጥንቃቄ ከተቀዳና ከተያዘ የዝናብውሃ እንዲሁም በንጽሕና ከተያዘ የምንጭ ውሃ ነው፡፡

**የውሃ ጥቅም፡-**

ውሃ ለምን ለምን ይጠቅማል?

- ለመጠጥና ምግብ ለማዘጋጀት
- ንጽሕናን ለመጠበቅ

- ለእርሻ ሥራ፣ ወዘተ. ይጠቅማል፡፡

ልጆች! ያለ ውሃ መኖር የሚቻል ይመስላችኋል?




ለመጠጥ



ምግብ ለማዘጋጀት


ሕይወት ያላቸው ነገሮች ያለውሃ ሊኖሩ አይችሉም።




እንስሳት ውሀ ያስፈልጋቸዋል።



እጽዋት ውሃ ያስፈልጋቸዋል።



ውሀ የገላን /የሰውነት/ ንጽሕናን ለመጠበቅ ይጠቅማል።



ውሀ ልብስ ለማጠብ ይጠቅማል።




ውሃ የምግብ ዕቃዎች ለማፅዳት ይውላል፡፡

ሥዕል 4.12 የውሀ ጥቅም

## ውሀን በንፅሕና መያዝ

ውሀ እንዴት ሊበከል ይችላል? ለመምህራችሁ ዘርዝራችሁ ተናገሩ፡፡


ውሀ በተለያዩ መንገዶች ሊበከል ይችላል፡፡




ሥዕል 4.13 የውሃ ብክለትን የሚያመጡ ነገሮች።

የውሀን ንጽሕና እንዴት እንጠብቃለን?

ውሀን በንጽሕና መያዝ ለጤናችን በጣም አስፈላጊ ነው።



ውሀን ማጣራት



ውሀን ማፍላት



ውሀን ከድኖ ማስቀመጥ

ሥዕል 4.14 ውሀን በንጽሕና መጠበቅ

### 4.2.3. አፈር

አፈር በየአካባቢው በመሬት ላይ የሚገኝ ሲሆን አፈርን በቅርፅና በቀለም መለየት ይቻላል፡፡

በቅርፅ

- አሸዋማ አፈር
- የሸክላ አፈር
- ደቃቅ አፈር በመባል ይታወቃሉ፡፡

በቀለም


- ቀይ አፈር
- ጥቁር አፈር
- ዳለቻ አፈር

**የአፈር ጥቅም**

-ለግብርና

እፅዋት ምግባቸውን የሚያገኙት ከየት ነው?

እፅዋት ምግባቸውን ሊያገኙ የሚችሉት ከአፈርነው፡፡ አፈር ውሃንና አየርን ስለሚይዝ ለተክሎች ምግብ ይጠቅማል፡፡ ተክሎች ቀጥ ብለው እንዲቆሙ የሚያደርጋቸው አፈር ነው፡፡



ሥዕል 4.15 አፈር ለግብርና የሚሰጠው ጥቅም

- ለቅርፃ ቅርፅ

ከሸክላ አፈር ምን ምን ዕቃዎች ይሰራሉ?



ሥዕል 4.16 ከአፈር የተሰሩ ቁሳቁሶች

ከስዕሉ ምን ተረዳችሁ?

አፈር ለእፅዋት ምግብየሚሆኑ ነገሮችን ይይዛል፡፡

- አፈርለቤትመስሪያ ይጠቅማል
- ከሸክላ አፈር የተለያዩ የቤት እቃዎችን መስራት ይቻላል፡፡

**የሸክላ አፈር ለቁሳቁስ መስሪያ እንዴት ይዘጋጃል?**

**ተግባራዊ ክንዋኔ 4.2**

ለተግባራዊ ክንዋኔ የሚያስፈልጉ ነገሮች፡፡

- ደቃቅ የተፈጨ የሸክላ አፈር
- የማቡኪያ ዕቃ

- የውሃ መጨመሪያ /ጣሳ/

የተግባራዊ ክንዋኔ ቅደም ተከተል


- የተፈጨውን የሸክላ አፈር ሰፋ ባለ እቃ ላይ አድርጎ ውሃ በመጨመር ማቡካት
- ትንሽ ትንሽ ውሃ እየጨመሩ ማሸት
- በጠፍጣፋ እቃ ላይ በእጅ ማድቦልቦል
- ሥዕሉን በማየት በቅደም ተከተል ከተዘጋጀ በኋላ የሚፈልጉትን አይነት ቅርፅ መስራት ይቻላል፡፡



ሀ. ውሃ መጨመር




ለ. ማቡካት




ሐ. ማድቦልቦል /ቅርፅ ማስያዝ/

ሥዕል 4.17 ከሸክላ ጭቃ ቁሳቁስ መስራት

ከሸክላ አፈር የተለያዩ ነገሮች ማዘጋጀት ይቻላል።



ከሸክላ የሚሰሩ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች




ከሸክላ የሚሰሩ ጌጣጌጦች

ሥዕል 4.18 ከሸክላ አፈር የሚሰሩ ቁሳቁሶችና ጌጣጌጦች

**የአፈር እንክብካቤ**

አፈር በጎርፍ ውሀ ታጥቦ እንዳይወሰድ ምን ማድረግ አለብን?




ሥዕል 4.19 አፈርን መንከባከብ

የአፈርን መሸርሸር ለመከላከል የሚያስፈልገው /ሊደረግ የሚገባው/ ዘዴ ፡-

- እርከን መስራት
- የዛፍ ችግኝን መትከል

  ምክንያቱም የዛፍ ስር አፈሩን አቅፎ ስለሚይዘው ነው፡፡

- መሬትን አግድም ማረስ
- አፈርላይ የሚበቅለውን ሳር በከብቶችከመጠን በላይ አለማስጋጥ ናቸው፡፡



አግድም በማረስ አፈርን መንከባከብ                    እርከን በመስራትአፈርን መንከባከብ

ሥዕል 4.20 አግድም በማረስና እርከን በመስራት አፈርን መንከባከብ

**መልመጃ 4.2**

**ሀ/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን “ሀሰት” በማለት መልሱ፡፡**

1. ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ያድጋሉ፡፡
2. የምንጠጣው ውሃ ንፁህ መሆን አለበት፡፡
3. ከአፈር ቤት መስራት ይቻላል፡፡
4. አፈር ለእፀዋት ምግብነት አያገለግልም፡፡
5. የመኪና ጐማ አገልግሎት የሚሰጠው አየር ከተሞላ ነው፡፡

**ለ/ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

6. ከአፈር ያልተሰራው የቱ ነው?

ሀ. ጀበና ለ. መኪና ሐ. ምጣድ

7. ከሚከተሉት አንዱ የውሃ መገኛ ነው፡፡

ሀ. ዝናብ ለ. ምንጭ ሐ. ሁሉም

8. የውሀን ንጽሕና ለመጠበቅ ምን ማድረግ አለብን?

ሀ. ማጣራት ለ. ማፍላት ሐ. ሁሉም

9. አፈር በጎርፍ ውሃ ታጥቦ እንዳይሄድ ምን ማድረግ አለብን?

ሀ. የዛፍ ችግኝ መትከል ለ. ሳሩን በከብቶች በጣም ማስጋጥ

ሐ. ቁልቁል ማረስ

10. ከሚከተሉት አንዱ የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡

ሀ. አየር ለ. ውሃ ሐ. ሁሉም

### 4.3. በአካባቢያችን የሚገኙ ሕይወት ያላቸው ነገሮች

| መታወቅ የሚገባቸው ቃላት | |
|---|---|
| - ቁጥቋጦ | - ጥበቃ |
| - ማከማቸት | - መኳኳዣ |
| - በርጩማ | - መዋለድ |
| - አእዋፍ | - ነፍሳት |
| - የዱር እንስሳት | |
| - ለማዳ | |

ሕይወት ያላቸው ነገሮች በሁለት ይመደባሉ፡፡ እነሱም፡-

1. እፅዋት እና
2. እንስሳት ናቸው፡፡

ሕይወት ያላቸው ነገሮች፡-


ሀ. ይመገባሉ

ለ. ያድጋሉ


ሐ. ይተነፍሳሉ


መ. ይንቀሳቀሳሉ፡፡

ሀ. ሕይወት ያላቸው ነገሮች ይመገባሉ።











ሥዕል 4.21 ሕይወት ያላቸው ነገሮች ይመገባሉ።


ለ. ሕይወት ያላቸው ነገሮች ያድጋሉ።




ጥጃ




ላም



ያላደገ ተክል



ያደገ ተክል




የዶሮ ጫጩት



ሥዕል 4.22 ሕይወት ያላቸው ነገሮች ያድጋሉ


ሐ. ሕይወት ያላቸው ነገሮች ይተነፍሳሉ፡፡

- የእነስሳት የመተንፈሻ አካላት
    - ሳንባ
    - አፍንጫ
    - ስንጥብ
    - የሰውነት ቆዳ ቀደዳና የመሳሰሉተ ናቸው፡፡



ሥዕል 4.23 ሕይወት ያላቸው ነገሮች ይተነፍሳሉ።

መ. ሕይወት ያላቸው ነገሮች ይንቀሳቀሳሉ።




ሥዕል 4.24 እንስሳት ይንቀሳቀሳሉ፡፡


አካባቢያችሁ ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ዘርዝሩ፡፡


### 4.3.1. እጽዋት

#### እፅዋትን መመደብ

በየአካባቢው የተለያዩ የእፅዋት አይነቶች ይገኛሉ፤ እነሱም፡-

- ትልልቅ ዛፎች
- ትንንሽ ዛፎች
- ቁጥቋጦዎች
- ረገኸርምና አጫጭር ሳር ናቸው፡፡





4.25. እፅዋት በአይነታቸው ይለያያሉ፡፡


እፅዋት- ለምግብነት የሚውሉና

- ለምግብነት የማይውሉ ተብለው ይመደባሉ፡፡


የሚከተሉትን ሥዕሎች በማየት ለምግብነት የሚውሉና ለምግብነት የማይውሉ በማለት ለዩዋቸው፡፡




እንሰት




የበቆሎ ተክል



ሙዝ




ሳር



ዕድ

ሣዕለ 4.26 ለምግብነት የሚውሉና የማይውሉ እፅዋት




ሥዕል 4.27 የእፅዋት ዋና ዋና ክፍሎች

የእፅዋት ዋና ዋና ክፍሎች የሚባሉት ፡-

- ሥር
- ግንድ
- ቅጠል
- ቅርንጫፍ ናቸው፡፡

**ሥር ፡-**

- ሥር በአፈር ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ከአፈር ውስጥ የእፅዋትን ምግብ /ውሃ፣ አየርንና ማዕድናትን/ ወደ ግንድ ያስተላልፋል፡፡ እንዲሁም በአፈረ ላይ ቀጥ ብሎ እንዲቆም ይረዳዋል፡፡

**ግንድ፡-** ከአፈር በላይ በኩል የሚገኝየዛፍ ክፍል ነው፡፡ የተክሉ ምግብ ያከማቻል፤ ወደ ቅርንጫፍና ቅጠል ያስተላልፋል፡፡

**ቅጠል፡-** የተክሉን ምግብ ያዘጋጃል፡፡

**የእፀዋት ጥቅም**

እፀዋት ለምን ለምን እንደሚጠቅሙ ታውቃላችሁ?

ሀ. እፀዋት ለምግብነት ይጠቅማሉ፡፡




እፀዋት ለሰው ልጅ ምግብነት ይውላሉ፡፡ እፀዋት ለእንስሳት ምግብነት ይውላሉ፡፡


ሥዕል 4.28 እፀዋት ለምግብነት ይጠቅማሉ፡፡

ለምግብነት የሚውሉ የእፀዋት አይነቶች፡-


1. የአትክልት ምግቦች
2. የፍራፍሬ ምግቦች
3. ሰብሎች ወይም እህልና ጥራጥሬ ተብለው ይታወቃሉ፡፡




ሥዕል 4.29 የአትክልት ምግቦች




ሥዕል 4.30 የፍራፍሬ ምግቦች





ሥዕል 4.31 የእህል አይነቶች

ለ/ እፅዋት ልብስ ለመስራት ያገለግላሉ።





ሥዕል 4.32 ከጥጥ የተሰሩ የተለያዩ ልብሶች

ሐ. እፅዋት ለቤትና የቤት ቁሳቁስ ለመስሪያ ያገለግላሉ።



መኖሪያ ቤት




ጠረጴዛና ወንበር

እጽዋት ለግቢ ውበት ለአጥር ይጠቅማሉ።



በርጩማ




አልጋ

ሥዕል 4.33 እፅዋት ለቤት ቁሳቁስ መስሪያ ይውላሉ።

መ/ እፅዋት ለእንስሳት መጠለያ ያገለግላሉ።



ሥዕል 4.34 አእዋፋትና የዱር እንስሳት በደን ውስጥ



ሥዕል 4.35 እፅዋት ለማገዶነት ይጠቅማሉ።

ልጆች! እፀዋትን ለማገዶነት ለመጠቀም ስንቆርጥ በምትካቸው ዛፎችን መተካት አለብን፡፡

**የእፀዋት መለያ ባሕሪያት**

የእፀዋት መለያ ባሕሪያት የምንላቸው፡-


- ይራባሉ
- ይመገባሉ
- ያድጋሉ፡፡

## የእፀዋት መራባት


እንደ እንስሳት ሁሉ እፀዋትም ይራባሉ፡፡
የሚራቡትም በዘር ወይም ግንዳቸው ተቆርጦ ሲተከል ነው፡፡




የበቆሎ ተክል በዘር ይራባል።



የሙዝ ተክል ግንዱ ተቆርጦ ይራባል።






የአተር ተክል በዘር ይራባል፡፡ የጽጌሬዳ ተክል ግንዱ ተቆርጦ ይራባል፡፡

ሥዕል 4.36 እፀዋት ይራባሉ፡፡

## የእፀዋት አመጋገብ፤

እፀዋት ይመገባሉ፡፡
እፀዋት ምግባቸውን ያዘጋጃሉ፡፡
እፀዋት ምግባቸውን የሚያዘጋጁት

- ከአየር
- ከፀሐይ ብርሃንና
- ከውሃ ነው፡፡



ሥዕል 4.37 እፀዋት ምግባቸውን ያዘጋጃሉ፡፡

## የእፀዋት ማደግ



እፀዋት በሚመገቡት ምግብ ያድጋሉ፡፡

ሥዕል 4.38 እፀዋት ያድጋሉ፡፡

## እፀዋትን መንከባከብ

በአካባቢያችሁ እፀዋትን ትንከባከባላችሁ? ለምን?

እፀዋት በሕይወት እንዲኖሩ መንከባከብ አለብን፡፡ የምንከባከበውም ከተተከሉ ጀምሮ ውሀ በማጠጣት ፣ በማረም፣ ማዳበሪያ በመጨመርና በእንስሳት እንዳይበሉ በመጠበቅ ነው፡፡





ሥዕል 4.39 እፀዋትን መንከባከብና መጠበቅ

እፀዋትን ካልተንከባከብናቸው ይሞታሉ፡፡ እፀዋትን ያለአግባብ መቅጠፍ ወይም መቁረጥ ተገቢ አይደለም፡፡

### 4.3.2. እንስሳት

**የእንስሳት አመዳደብ**


እንስሳት በሁለት ይመደባሉ፤ እነርሱም፡-

1. የቤት እንስሳት /ለማዳ/ና
2. የዱር እንስሳት ናቸው፡፡

1. **የቤት እንስሳት፡-** የቤት እንስሳት ለማዳ እንስሳት ናቸው፡፡ ሰው በሞኖሪያ ቤቱ አካባቢ ይገለገልባቸዋል፡፡
2. **የዱርእንስሳት**

የዱር እንስሳት ማለት ምን ማለት ነው?

የዱር እንስሳት ማለት ከሰው ርቀው በጫካ ውስጥ የሚኖሩ ማለት ነው፡፡



አንበሳ

ከእነዚህ ከሚታዩ ስዕሎች


ሀ/ በቤት ውስጥ የሚኖሩ

1 ____________________


2 ____________________

3 ____________________

4 ____________________



ላም




ድመት



ውሻ

**በስዕሉ ላይ የሚታዩት እንስሳት የት ይኖራሉ?**




ሥዕል 4.40 እንስሳት በመኖሪያ አካባቢያቸው ሲመደቡ

## የእንስሳት አገልግሎት

1. የቤት እንስሳት ጥቅም

ሰዎች የሚገለገሉባቸው የቤት እንስሳት፡-

ሀ/ ለምግብነት


ለ/ ለጥበቃ

ሐ/ ለዕቃ ማጓጓዣነት


መ/ ለልብስና ለጫማ መስሪያ ያገለግላሉ፡፡

ሀ/ ለምግብነት


ለምግብነት የሚውሉ የቤት እንስሳት እነማን ናቸው?



የወተት ላም




ዶሮ



በግ

ለ. ለጥበቃ

ለጥበቃ የሚያገለግሉ እንስሳት የትኞቹ ናቸው?






ሥዕል 4.41 እንስሳት ለጥበቃ ያገለግላሉ፡፡

### ሐ/ እቃ ለማጓጓዝ

እንስሳት እቃ ከቦታ ወደ ቦታ ለማጓጓዝ ይጠቅማሉ፡፡




ሥዕል 4.42 ለእርሻና ለማጓጓዣነት የሚያገለግሉ እንስሳት


### መ/ የእንስሳት ቆዳ ጥቅም

የእንስሳት ቆዳና ሌጦ ፡-

- ለጫማ
- ለልብስ
- ለቦርሣና
- ለቀበቶ መስሪያ ያገለግላል፡፡

የእንስሳት ቀንድ ለጌጣጌጥና ለቤት መገልገያ ቁሳቁስ መስሪያነት ያገለግላል፡፡





ፀጉራቸውም ለልብስ መስሪያነት ያገለግላል፡፡


ሥዕል 4.43 የእንስሳት ቆዳ አገልግሎት

## 2. የዱር እንስሳት ጥቅም


እንስሳት የተፈጥሮ ውበትና የገቢ ምንጭ እንደሆኑ ታውቃላችሁ? በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ እንስሳት እነማን እንደሆኑ ታውቃላችሁ? የሚከተሉትን ስዕሎች ተመልከቱ፡፡



ዋሊያ



ኒያላ



የሰሜን ቀይ ቀበሮ



ጭላዳ ዝንጀሮ

ሥዕል 4.44 በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ብርቅዬ እንስሳት

በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ አእዋፋት እንዳሉ ታውቃላችሁ?

በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ አእዋፋት 23 ሲሆኑ ከ23ቱ መሀከል ጥቂቶቹ ስዕላቸውን በመመልከት እወቋቸው፡፡



ሥዕል 4.45 በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ አእዋፋት

**የእንስሳትባሕርያት ፡-**

ሀ/ እንስሳት ይዋለዳሉ ወይም ይራባሉ፡፡

ለ/ እንስሳት ይተነፍሳሉ፡፡

ሐ/ ይንቀሳቀሳሉ፡፡

መ/ ያድጋሉ ፡፡ ሠ/ ይመገባሉ፡፡

ሀ/ የእንስሳት መራባት

እንስሳት ይዋለዳሉ ወይም ይራባሉ፡፡


የሚራቡትም እንቁላል በመጣል ወይም መሰላቸውነ በመውለድ ነው፡፡




ሥዕል 4.46 እንስሳት ይራባሉ፡፡

### ለ/ የእንስሳት መተንፈስ


እንስሳት የሚተነፍሱባቸው የሰውነት ክፍሎች የተለያዩ ናቸው፡፡




ሰው በሳንባው ይተነፍሳል።



አሣ በስንጥቡ ይተነፍሳል።





ነፍሳት በሰውነታቸው ላይ ባሉ ቀዳዳዎች ይተነፍሳሉ፡፡

ሥዕል 4.47 የእንስሳት መተንፈሻ አካል

**መልመጃ 4.3**


ባዶ ቦታዎችን ሙሉ፡፡

1. ሰው በ_______________ ይተነፍሳል፡፡
2. አሳ በ________________ ይተነፍሳል፡፡
3. ትናንሽ ነፍሳት በ______ ይተነፍሳሉ፡፡

### ሐ/የእንስሳ ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር

እንስሳት ምግብና መኖሪያ ፍለጋ ከቦታ ወደ ቦታ ይንቀሳቀሳሎ፡፡ ይኸውም፡-

- በእግራቸው በመራመድ
- በክንፋቸው በመብረር
- በደረታቸው በመሳብና
- ከቦታ ቦታ በመዝለል ይሄዳሉ፡፡




ሥዕል 4.48 እንስሳት ይንቀሳቀሳሉ፡፡

ተማሪዎች! ሕይወት ባላቸውና በሌላቸው ነገሮች መካከል የሚታዩትን ልዩነቶች መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ በቀረበው ምሳሌ ባሕሪያቸውን “አይደለም” ወይም “**አዎ**” በማለት ባዶ ቦታዎቹን ሙሉ፡፡

ሠንጠረዥ 4.1

| ባሕሪያት | ሕይወት ያላቸው ነገሮች | ሕይወት የሌላቸው ነገሮች |
|---|---|---|
| ይመገባሉ | አዎ | አይደለም |
| ይተነፍሳሉ | | |
| ያድጋሉ | | |
| በራሳቸው ይንቀሳቀሳሉ | | |
| ይራባሉ | | |


## የእንስሳት እንክብካቤ





የቤት እንስሳት ምግብና ውሃ ይፈልጋሉ።





የቤት እንስሳት መንከባከብ ማለት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?

የቤት እንስሳት ንጽሕና መጠበቅ አለበት፡፡

ሥዕል 4.49 እንስሳትን መንከባከብ

ስለዚህ የቤት አንስሳትን መንከባከብ አንጂ ማሰቃየት ተገቢ አይደለም፡፡ ለምሳሌ፡- ውሻን ማባረር፣ ድመትን መደብደብ ተገቢ አይደለም፡፡

የዱር እንስሳት እራሳቸው ቢመገቡም የሚኖሩበትን አካባቢ በመጠበቅና በጥንቃቄ በመያዝ መንከባከብ አለብን፡፡ ለምሳሌ ፡- በሚኖሩበት ጫካ ዛፎችን ባለመቁረጥ፣ ዛፎችን በመትከል፣ ወዘተ. ሊሆን ይችላል፡፡

**መልመጃ 4.4.**

**ሀ/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን “ሀሰት” በማለት መልሱ፡፡**

1. ሕይወት ያላቸው ነገሮች አይንቀሳቀሱም፡፡
2. እፅዋት ለእንስሳት መጠለያ ናቸው፡፡
3. በቅሎ ለመጓጓዣነት ያገለግላል፡፡
4. እንሰት ለምግብነት አይውልም፡፡
5. አንበሳ የቤት እንስሳ ነው፡፡

**ለ/ ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

6. እንስሳት ከሚሰጡት ጥቅም አንዱ ____________ ነው፡፡

   ሀ/ ለምግብነት ለ/ ለጥበቃ ሐ/ ሁሉም

7. ዶሮ ________ ትጥላለች፡፡

   ሀ/ ልጅ ለ/ እንቁላል ሐ/ ጫጩት

8. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የዱር እንስሳት ጥቅም ነው፡፡

   ሀ/ ለገቢ ምንጭ ለ/ እቃ ለማጓጓዝ ሐ/ ለቤት ጥበቃ

9. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ እንሰሳ ነው፡፡

   ሀ/ ወሊያ ለ/ ኒያላ ሐ/ ሁሉም

10 . እንስሳትን ምን ምን በማድረግ እንከባከለን?

   ሀ/ ከቦታ ቦታ በማባረር ለ/ በማሳቃየት

   ሐ/ ምግብና ውሃ በመስጠት

**ሐ/ ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡**

11.እንስሳት ለምን ከቦታ ቦታ ይዘዋወራሉ?

12. ሰው በቤት አካባቢ የሚገለገልባቸው እንስሳት ምን ይባላሉ?

## 4.4 በአካባቢያችን የሚደረጉ የተለመዱ እንቅስቃሴዎች

| መታወቅ የሚገባቸው ቃላት | |
|---|---|
| - ሽመና | - ጊዜ |
| - ስራ | - አግባብ |
| - ሸክላ | - ሐኪም |
| - ፋብሪካ | - ዕቅድ |
| - ክብር | |

### 4.4.1. የሥራ ጥቅም

ሥራ ለምን ይጠቅማል?

ዋነኛው የሥራ ጥቅም የገቢ ምንጭ ማስገኘት ነው፡፡

ይህም ከሥራ በሚገኘው ገንዘብ ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ለማግኘት ያስችለናል፡፡

ሰዎች በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተው ሥራ ካልሰሩ ኑሮዋቸውን በአግባቡ መምራት አይችሉም፡፡

### 4.4.2. የስራ አይነቶች

ልጆች! በአካባቢያችሁ ሰዎች ምን ምን በመስራት ይኖራሉ?

የሥራ አይነቶች ሲመደቡ፡-

- የግል ሥራ
- ለመንግሥት ተቀጥሮ መስራትና
- ለሰዎች ተቀጥሮ መስራት ናቸው፡፡

**የግል ሥራ**

ሰዎች በግል ሥራ ሊሰማሩ የሚችሉት

- በግብርና

- በንግድ
- በሽመና
- በሸክላ ስራና በመሳሰሉት ነው፡፡


**ግብርና**

በገጠር የሚኖሩ አብዛኛዎቹ ሰዎች መሬት በማረስና እህል በማምረት ይኖራሉ፡፡ በተጨማሪ ከብት በማርባት ፣ በሸክላ ሥራና በንግድ ሥራ የሚተዳደሩ አሉ፡፡

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ የግብርናንና የንግድ ስራን አጣምሮ በመስራት ይኖራሉ፡፡




ሥእል 4.50 በገጠር የሚኖሩ ሰዎች በግብርና ይተዳደራሉ፡፡



ሥዕል 4.51 ዘመናዊ የግብርና ሥራ


በዘመናዊ የግብርና አስተራረስ ሰፋፊ ቦታዎችን በማልማት ጥቅም ላይ አውሎ ረሀብና ችግርን ከሀገራችን ማጥፋት ይቻላል፡፡



ሥዕል 4. 52 የሸክላና የብረታ ብረት ሥራ

በከተማ የሚኖሩ ሰዎች ምን ምን በመስራት ይኖራሉ?


ሰዎች አገልግሎት ሰጪ በሆኑ በመነግሥት መስሪያ ቤቶች ወይም በአንድ የግል ድርጅት



ተቀጥረው በመስራት የወር ደመወዝ በማግኘት ይተዳደራሉ፡፡

ሥዕል 4.53 መማርና ማስተማር የሥራ አይነቶች ናቸው፡፡

ተማሪዎች የእናንተ ሥራ ምንድን ነው?




የመምህራንስ ሥራ ምን ይመስላችኋል?

ሥዕል 4.54 በሽመና የሚተዳደሩ ሰዎች

አንዳንድ ሰዎች ልዩ ልዩ ልብሶችን ሰርተው ይለብሳሉ፡፡ በመሸጥም ኑሮዋቸውን ሊመሩ ይችላሉ፡፡

ልብስ በመስራትና በመሸጥ መሰረታዊ ፍላጐቶቻቸውን የሚያሟሉ ሰዎች ምን ይባላሉ?



ሥዕል 4.55 በፋብሪካ ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰዎች


ሰዎች በጨርቃጨርቅ፣ በዱቄት ፋብሪካዎች፣ በሳሙና ፌብሪካዎች፣ በብረታብረት ፋብሪካዎችና በመሳሰሉት በመስራት ኑሮአቸውን ሊመሩ ይችላሉ፡፡

ልጆች! በአካባቢያችሁ ፋብሪካዎች አሉን? ካሉ ምን ምን የሚያመርቱ ናቸው?



ሥዕል 4.56 ሰዎች ቤት ሲሰሩ

ቤት በመስራትና አጥር በማጠር የሚተዳደሩ ሰዎች ምን ይባላሉ?




ሥዕል 4.57 በጥበቃ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች

በአካባቢያችሁ ፀጥታን በማስከበር ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ምን በመባል ይታወቃሉ?

አንዳንድ ሰዎች እቃዎችን በመሸጥና በመግዛት ይተዳደራሉ፡፡

ተማሪዎች! እነዚህ ሰዎች ምን ይባላሉ?




ሥዕል 4.58 ልዩ ልዩ የንግድ ሥራዎች

በአካባቢያችሁ የሚሰሩ የንግድ አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

ሥራ መሰረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት እና አካባቢን አልምቶ ለመጠቀም እጅግ አሰፈላጊ ነው፡፡


### 4.4.3. የሥራ ክቡርነት

ማንኛውም ሥራ ክብር ሊሰጠው ይገባል፡፡ ሥራን ማክበር ደግሞ ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀምና ሥራን በእቅድ ለመምራት ያስችላል፡፡

ሰዎች ሥራ በሚሰሩበት ጊዜ ጊዜያቸውን በአግባቡ መጠቀም አለባቸው፡፡ ለምሳሌ የተመደበለትን ሰዓት በአግባቡ በመጠቀም ለስራው ታማኝና ቅን መሆን ያስፈልጋል፡፡

ጊዜን በአግባቡመጠቀም

ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት በጊዜ ለመሄድ ሰዓትን አክብሮ መገኘት ያስፈልጋል፡፡




4.59 ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም የትምህርተ ሰዓትን ያባክናል፡፡

አርፍዶ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት ሥንፍና ነው፡፡

ጐበዝ ተማሪዎች ጠዋት ተነስተው ፊታቸውን ታጥበው፣ ቁርሳቸውን በመብላት የትምህርት ክፍለ ጊዜ ሳይደርስና ሳያረፍዱ ወደ ትምህርት ቤት በመሄድ የሰንደቅ አላማ ስነስርዓትን አክብረው ትምህርታቸውን ይከታተላሉ፡፡

ተማሪዎች! እናንተስ የሰንደቅ አላማ ስነስርዓት ታከብራችሁ?



ሥዕል 4.60 የትምህርት ሰዓት ሳያልቅ መውጣት የስንፍና ምልክት ነው፡፡

የትምህርት ሰዓትአክብሮ እስከ መጨረሻው ክፍለ ጊዜ መማር የጎበዝ ተማሪዎች ተግባር ነው፡፡

ተማሪዎች! የትምህርት ሰዓት ታከብራላችሁ?

ትምህርት ሳይጀመር ትምህርት ቤት በመድረስ የሰንደቅ አላማ ሥነስርአት አክብራችሁ እስከ መጨረሻው ትማራላችሁን?

- በአካባቢያችሁ መሬት የሚታረሰው በምን በምን ወራት ነው?


- የተዘራው ሰብል ደርሶ ምርት



የሚሰበሰበው በምን ወርነው?

ሥዕል 4.61 የግብርና ሥራን በወቅቱ ማከናወን

ገበሬዎች በእርሻ ወቅት አርሰው ይዘራሉ፡፡ አንድ ገበሬ በወቅቱ አርሶ በወቅቱ ካልዘራ ጥሩ ምርት አያገኝም፡፡



ሥዕል 4.62 ሀኪሞች በሕክምና ስራ ላይ

ሀኪሞች በሀኪም ቤቶች የሥራ ሰዓት አክብረው ባይሰሩ ምን ችግር ይፈጠራል?

የሥራና የቀጠሮ ሰዓት አክብሮ በመገኘት ከአንድ ሰው የሚጠበቅ ጥሩ ስነምግባር ነው፡፡

### ሥራን በእቅድ መምራት

ሥራን በእቅድ መምራት ውጤታማ ያደርጋል፡፡ በአንድ ቀን ውስጥ የምንሰራውን ሥራ በሰዓት ከፋፍሎ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ ይኸውም፡- የጥናት ጊዜ፣ የጨዋታ ጊዜ፣ ቤተሰብን በስራና በመላላክ የመርዳት ጊዜ በማለት ከፋፍሎ መጠቀም ይቻላል፡፡

ከዚህ በታች በተገለፀው ሰንጠረዥ መሠረት በየእለቱ የምታከናውኑትን ተግባር በጊዜ ከፋፍላችሁ ተጠቀሙ፡፡

| ተ/ቁ | የሳምንት ቀናት | የሚከናወኑ ተግባራትና ሰዓት | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ትምህርት ቤት | ለጥናት | ለጨዋታ | ቤተሰብ ለመርዳት | |
| 1 | ሰኞ | | | | | |
| 2 | ማክሰኞ | | | | | |
| 3 | ረቡዕ | | | | | |
| 4 | ሐሙስ | | | | | |
| 5 | አርብ | | | | | |
| 6 | ቅዳሜ | | | | | |
| 7 | እሁድ | | | | | |

ሠንጠረዥ 4.2 ጊዜ ሳይባክን በእቅድ ከፋፍሎ መጠቀም

**መልመጃ 4.5**

**ሀ. ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. ዋነኛው የሥራ ጥቅም የገቢ ምንጭ ማስገኘት ነው፡፡
2. ሥራ መስራት መሰረታዊ ፍላጐቶችን ለማሟላት አይጠቅምም፡፡
3. ሰዎች ሥራን ሲሰሩ ጊዜያቸውን በአግባቡ መጠቀም የለባቸውም፡፡

**ለ. ከተሰጡት አማራጮች መሀከል ትክክለኛውነ መልስ ምረጡ፡፡**

4. አርፍዶ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት ________ ምልክት ነው

ሀ/ የጐበዝ ተማሪ ለ/ የሰነፍ ተማሪ ሐ/ ሁሉም

5. ልብስ በመስራት የሚተዳደሩ ሰዎች ምን ይባላሉ?

ሀ/ አንጥረኛ ለ/ ሸማኔ ሐ/ አናፂ

## 4.5. መጓጓዣዎች

| መታወቅ የሚገባቸው ቃላት |
|---|
| - ዘመናዊ<br>- ባሕላዊ<br>- የብስ<br>- ጭነት<br>- ሐዲድ<br>- አውቶብስ |

ተማሪዎች! መጓጓዣ ማለት ምን ማለት ነው?

መጓጓዣ ማለት ሰውን ወይም እቃን ከቦታ ቦታ የምናንቀሳቅስበት ነገር ማለት ነው፡፡

ሁለት አይነት መጓጓዣዎች አሉ፤ እነሱም፡-

1. ባሕላዊ መጓጓዣዎችና

2. ዘመናዊ መጓጓዣዎች ናቸው፡፡


### 4.5.1 ባሕላዊ መጓጓዣዎች

ባሕላዊ መጓጓዣዎች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ፡፡


በባሕላዊ መጓጓዣዎች ራቅ ወዳለ ሥፍራ ሄዳችሁ ታውቃላችሁ?



በቅሎ



የአህያ ጋሪ



ግመል

ሥዕል 4.63 ልዩ ልዩ ባሕላዊ መጓጓዣዎች


### 4.5.2 ዘመናዊ መጓጓዣ

ልጆች ወደ ትምህርት ቤት በምን ትጓዛላችሁ?


- በእግር
- በአህያ ጋሪ

- በመኪና
- በፈረስ ጀርባ
- በፈረስ ጋሪ
- በብስክሌት


ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ ዘመናዊ የመጓጓዣ አይነቶች የትኞቹ ናቸው?



ሳይክል




አውሮኘላን




የጭነት መኪና



መኪና



ባቡር



መርከብ

ሥዕል 4.64 ዘመናዊ መጓጓዣ አይነቶች

**የመጓጓዣ ጥቅም**

መጓጓዣ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

- መጓጓዣ ከተጠቀምን ሩቅ መንገድ ሳይደክመን መሄድ እንችላለን፡፡
- ምቾች ይሰጠናል፡፡
- እኛ ልንሸከም የማንችለውነ ከባድና ብዙ ዕቃ በቀላሉ እናጓጉዛለን፡፡
- በፍጥነት ያደርሰናል፡፡

መጓጓዣዎችን ፡-

- በአየር የሚሄድ
- በውሃ የሚሄድና
- በየብስ /በደረቅ መሬት/ የሚሄድ ብለን እንከፍላቸዋለን፡፡

**በአየር ላይ የሚሄድ የመጓጓዣ አይነት**

በአየር ላይ የሚጓዝ የመጓጓዣ አይነት ምን ይባላል?




ሥዕል 4.65 የአየር መጓጓዣ

አውሮኘላን በጣም ረጅም ርቀትን በፍጥነት ለመድረስ የሚረዳ የመጓጓዣ አይነት ነው፡፡

**በውሀ ላይ የሚሄድ የመጓጓዣ አይነት**

በውሃ ላይ የሚሄድ የመጓጓዣ አይነት ምን ይባላል?




ሥዕል 4.66 የውሃ ላይ መጓጓዣ

መርከብ በውሀ ላይ መጓጓዣ ሲሆን ብዙ ጭነት ጭኖ ረጅም ርቀትን የሚጓዝ ነው፡፡


ጀልባ በሐይቅ እና በወንዞች ላይ የምንጠቀምበት መጓጓዣ ሲሆን ሰዎች አሳ ለማጥመድ እና ለመዝናናት ይጠቀሙበታል፡፡

በየብስ /በደረቅ መሬት/ የሚሄድ የመጓጓዣ አይነት

ደረቅ መሬት ላይ የሚሄዱ የመጓጓዣ አይነቶችን ዘርዝሩ ፡፡









ሥዕል 4.67 የየብስ /የደረቅ መሬት/ መጓጓዣ

ባቡር በሐዲድ ላይ ይጓዛል፡፡ ሰዎችንና ብዙ ጭነትን ለማጓጓዝ ይጠቅማል፡፡

የጭነት መኪና ብዙ እቃዎችን ለማጓጓዝ ይጠቅማል፡፡

አውቶብስ ሰዎችን ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ ይረዳል፡፡

በሚከተለው ሰንጠረዥ ባሉት ባዶ ቦታዎች ላይ ተስማሚ የሆነውን ሃሣብ ሙሉ ፡፡

ሰንጠረዥ 4.3

| | የመጓጓዣ አይነቶች | መጓጓዣዎች የሚጓዙበት መንገድ |
|---|---|---|
| ባሕላዊ መጓጓዣዎች | 1. አህያ | በየብስ |
| | 2. | |
| | 3. | |
| | 4. | |
| | 1. አውቶቡስ | በየብስ |

| | | |
|---|---|---|
| ዘመናዊ መጓጓዣዎች | 2. | |
| | 3. | |
| | 4. | |

**መልመጃ** 4.6

**ሀ. ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. መጓጓዣ ከተጠቀምን ሩቅ መንገድ ሳይደክመን መሄድ እንችላለን፡፡
2. በቅሎ ዘመናዊ መጓጓዣ ነው፡፡
3. መርከብ የውሃ ላይ መጓጓዣ አይነት ነው፡፡

**ለ. ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

4. በአየር ላይ የሚሄድ መጓጓዣ ምን ይባላል?
   ሀ/ አውሮኘላን ለ/ መርከብ ሐ/ መኪና
5. ዘመናዊ መጓጓዣ ከምንላቸው ውስጥ አንዱ ነው፡፡
   ሀ/ ፈረስ ለ/ በቅሎ ሐ/ ባቡር
6. ከሚከተሉት ውስጥ ፈጣን የሆነው መጓጓዣ የትኛው ነው?
   ሀ/ መርከብ ለ/ አውሮኘላን ሐ/ ሳይክል

**ማ ጠ ቃ ለ ያ**

- ከምትኖሩበት አካባቢ አንፃራዊ መገኛ ለማወቅ የፀሐይ መውጫ ምስራቅ ሲባል የፀሐይ መጥለቂያ ደግማ ምዕራብ ይባላል፡፡ ደቡብና ሰሜን የምንላቸውን አቅጣጫዎች ለማወቅ ፊታችንን ወደ ፀሐይ መውጫ አድርገን እጃችንን ወደ ጐንና ጐን ስንዘረጋ ቀኝ እጃችን የደቡብ አቅጣጫን ሲያመለክት የግራ እጃችን ደግሞ ሰሜንን ያመለክታል፡፡
- ሕይወት የሌላቸው ነገሮች የተፈጥሮ ሀብት ናቸው፡፡ እነዚህም አፈር፣ አየር፣ ውሃ፣ ድንጋይና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች አይመገቡም፣ አያድጉም፣ አይንቀሳቀሱም፣ አይተነፍሱም፡፡ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች በሦስት ይመደባሉ፤ እነሱም፡-

  ጠጣር ነገሮች፣ ፈሳሽ ነገሮች፣ ጋዞች / አየር/ ናቸው፡፡

- ሕይወት ያላቸው ነገሮች በሁለት ይመደባሉ፡፡ እነርሱም እጽዋትና እንስሳት ናቸው፡፡ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ይመገባሉ፣ ያድጋሉ፣ ይራባሉ፣ ይተነፍሳሉ፣ይንቀሳቀሳሉ፡፡

እጽዋትበሁለት ክፍል ይመደባሉ

1. ለምግብነት የሚውሉና
2. ለምግብነት የማይውሉ ናቸው፡፡

እንስሳት በሁለት ይመደባሉ፣ እነርሱም፡-

1. የቤት እንስሳት /ለማዳ/ እና
2. የዱር አንስሳት ናቸው፡፡

- ዋነኛው የሥራ ጥቅም የገቢ ምንጭ ማስገኘት ነው ፡፡ ከሥራ የሚገኘው ገንዘብ ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ ለማግኘት ያስችለናል፡፡
- መጓጓዣ ማለት ሰውን ወይም እቃን ከቦታ ቦታ የምናንቀሳቅስበት ነገር ማለትነው፡፡ ሁለት አይነት መጓጓዣዎች አሉ፡፡ እነርሱም፡- ባሕላዊ መጓጓዣና ዘመናዊ መጓጓዣዎች ናቸው

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. አየር የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡
2. ውሃ ሕይወት አለው፡፡
3. ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ይንቀሳቀሳሉ፡፡
4. የእንስሳት ቀንድ ለጌጣጌጥና ለቤት እቃዎች መስሪያ ያገግላል፡፡
5. መሬት ውስጥ ያለው የተክል ክፍል ሥር ይባላል፡፡

**ለ/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከ"ለ" ስርያሉትን ከ"ሀ" ስር ባሉት አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 6. የመኪና ጎማን ለመሙላት ያገለግላል | ሀ. እጽዋት |
| 7. ለመጠጥነት ይጠቅማል | ለ. አየር |
| 8. ለጉልበት ሥራ ይጠቅማሉ | ሐ. አፈር |
| 9. የእንጀራ ምጣድ ለመስራት ያገለግላል | መ. ውሀ |
| 10.የአእዋፋትና የዱር እንስሳት መጠለያነት ያገለግላል፡፡ | ሠ. እንስሳት |

**ሐ/ ከተሰጡት አማራጮች መሀከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

11.ከእህል /ከጥራጥሬ/ አይነቶች አንዱ ነው፡፡

ሀ. ፓፓዬ ለ. ጎመን ሐ. ስንዴ

12. እጽዋት ምግባቸውን የሚያዘጋጁት በ_________ ነው፡፡

ሀ. አየር ለ. ፀሐይ ብርሃን ሐ. ሁሉም መልስ ነው፡፡

13.የእጽዋት መለያ ባሕሪያት ምን ምን ናቸው?

ሀ/ ይራባሉ ለ/ ያድጋሉ ሐ/ ሁሉም ትክክል ነው፡፡

14. ከአፈር በላይ የሚገኘው የእጽዋት ክፍል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ ግንድ ለ/ ሥር ሐ/ ቅጠል

15.ባሕላዊ የመጓጓዣ አይነት የትኛው ነው?

ሀ/ በአህያ ማጓጓዝ ለ/ በፈረስ ማጓጓዝ ሐ/ ሁሉም ትክክል ነው፡፡